http://ethioliberty.wordpress.com/

የመሪ ሕሸት


D
AMH
ADMASU
DASTA

አድማሱ ደስታ

http://ethioliberty.wordpress.com/

የማር እሸት

ነባር ግጥሞች



ከአድማሱ ደስታ

ኢትዮጵያ መጻሕፍት ድርጅት
1980
Ethiopia Book Centre
1988

http://ethioliberty.wordpress.com/

ኢትዮጵያ መጻሕፍት ድርጅት
የ.ፖ.ሣ. ቁ. 1024 አዲስ አበባ

ETHIOPIA BOOK CENTRE
P. O. Box 1024 Addis Ababa

D
AP
3e

መብቱ ለልጎ የተጠበቀ ነው
ALL RIGHTS RESERVED

ንግድ ማተሚያ ቤት ታተመ
Printed by Commercial Printing Press

ማውጫ

መግቢያ 5
ክፍል አንድ—የፍቅር ግጥሞች 10
ክፍል ሁለት—የሐዘን ግጥሞች 41
ክፍል ሦስት—ግፍና በደል መገለጫ ግጥሞች 57
ክፍል አራት—የጀግንነት ግጥሞች 74

http://ethioliberty.wordpress.com/

መግቢያ

እንዚህን ስለምን ግጥሞች አከማችቼ በመጽሐፍ ቅጽ ለማሳተም ያነሣሣኝ ዋናው ምክንያት፣ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋን በማስተምርበት ጊዜ፣ ከመደበኛ ትምህርት ጣልቃ እያስገባሁ ያባቶቻችንንና የእናቶቻችንን ሽለላ፣ ቀኸራ፣ የፍትር እንጉርጉሮና የሐዘን ሙሾ ለተማሪዎች ስንገራቸው ከመጠን በላይ ይደሰቱ ስለነበር፣ ከዚያን ጊዜ እንሥቶ ማጠራቀም ጀመርሁ።

ዋናው ዓላማዬም፣ የዘመኑ ወጣት፣ በተለይ በትምህርት ዝቢታ ላይ የሚገኘው፣ እንዚህን ግጥሞች በማንበብ የሀገሩን ይትባህል አውቆ፣ በዚያን ጊዜ አባቶቻችንና እናቶቻችን ያስሟቸው የነበሩት የፍትር፣ የሐዘንና የደስታ እንዲሁም የጀብዱ ግጥሞች፣ ምን ያህል ተውህቦ እንደ ነበራቸው በዘመናችን ካሉት ጋር እያወዳደረ ምስጢራቸውን እንዲረዳ ለማድረግ ነው። ይኸውም የአማርኛን ቋንቋ የሚያጸብሩ ብዙ ቃላትና ሐረጎች ስለሚገኙባቸው ይጠቅማሉ። በእርግጥ የሰበሰብኳቸው ግጥሞች በር ከት ያሉ ነበሩ፣ ግን አንዱ የነገረኝን ሌላው መልሶ ስለሚነገረኝ በጣም የተለመዱትን አስቀርቼ እንጊዳ የሠሰሱኝንና ምስጢር አዘል የሆኑትን ብቻ ሰብስቤ ጽፌአለሁ። አንዳንዶቹን ግጥሞች ያነሃኋቸው ከልዩ ልዩ ክፍለ ሀገር መጥተው አዲስ አበባ ከሚኖሩ ሰዎች ሲሆን፣ ሌሎችን ግን እኔው ራሴ በመዘዋወር የሰበሰብኳቸው ናቸው።

በዚህ አጋጣሚ በ1964 ዓ.ም. በደብረ ማርቆስ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በብሔራዊ አገልግሎት ላይ በነበርኩበት ጊዜ፣ ከሰባቱም አውራጃዎች

http://ethioliberty.wordpress.com/

የመጡት ተግሪዎች ግዛሞችን በመሰብሰብ ስለ ረዱኝ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

እንዚህን የደስታም ሆኑ የሐዘን ስለምን ግጥሞች ጠለት ያለ ሚስጢርና ትምህርት ስላላቸው ፣ በለሆሳስ አንብቦ የፀንኑውን ከአበውና ከመምህራንአንዲሁም ከባል ቴቶች በመጠየቅ ውስጠ ሚስጢራቸውን ለመረዳት መሞከር አዋቂነት ነው ።

ትውልድ አልፎ ትውልድ ሲተካም ፣ ለተተኪው ትወ ልድ ያወርሳል ፣ ወራሹም ትውልድ በውርስ ያገኘው የአ በው መልካሙ ባህልና ፍልስፍና ለሥልጣኔ እርምጃው መመኪያ መሠረት ይሆንዋል ። በዚህ መሠረት በፊውዶ ቡርገው ሥርዓት ይማቅቅ የነበረው ኢትዮጵያዊ ፣ ፍትሕ ሲጓደልበት ፣ ሲበደል፣ አላግባብ በትንሽ በትልቁ ሲንገላታ እሮሮውን ቸኽለላ ፣ በቱከራ ፡ በዘፈን ፣ ቤሐዘን እንጉርጉሮ ይገልጽ ነበር ። በወግ እንዲያስተዳድሩት የተሾሙለት ገዥዎች አቤቱታውን ከምንም ባለመቁጠር እንደ ሊም ንት ስለሚመለከቱት ከማንጉራጉር እያመለሰም ነበር ። በየእያባባዩና በየጋራው እየሄደ አቤቱታውን በኽለላ ሲያሰማ መልስ የሚሰጠው የገደል ማሚቶ ብቻ ነበር ።

ሹሙም ሲበድለው ፡—

« እረ ጉራው እረ ጉራው ፣
ለምስለኔው ሙክት ለጭቃው ወጠጤ ፣
እንዲህ ሆኜ ነው ወይ ካገር መቀመጪ »

እያለ ሌላ እንኳ ባያደርግ ከአንዱ ከፍል ሀገር ወደ ሌላው ከፍል ሀገር ንብረቱን እየተመ የተንከራተተበት ጊዜው እሩት አልነበረም ።

ምን ማለት ነው ? ከላይ የጠቀስኩት ሕዝብ ለፊውዶ ጌታ ልግ ነበር ። ይደርስበት የነበረው በደል ከአቅሙ በላይ ሆኖ ሲያገኘው—በብስጭት ፡—

« ካገር እናር ብዬ ፣
ኩበት እንዳ ብዬ ፣
ልጅ አሳድግ ብዬ ፣
ለባሻ ዳርሁለት ሚስቴን አቴ ብዬ »

በግለት የተቃጠለ ብሶቱን ይገልጽ ነበር ። ግን ትዕግሥቱ ከመጠን አልፎ ራሱን መቈጣጠር ሲያቅተው — በፉ ከራ ፡—

« ከገደሉ አያቀር ቡታ ቡታውን ፣
ተዝካሩ ሳምንት የሚበላውን ።
ቢተባበሱ እንደ ቅቤ ቅል ፣
መተኩስና መግደል አየቅል ።
ቢተባበሱ እንደ ከርቾ ፣
መተኩስና መግደል ለብቻ »

እያለ ባገኘው መሣሪያ ዘርሰቶት ይሄድ ነበር ። ዝጠሬው ሕዝብ ወንድነትን ከጉብዝና ፣ ኩስታራነትን ከርኅራሄ ፣ ጀግንነትን ከቸርነት ጋር አስተባብሮ የያዘ ንጹሕ ኢትዮ ጵያዊ ፣ የሀገር ፍቅር እንደ አሳት ያቃጠለው ፣ ጊዜው በሚ ፈቅድለት መሣሪያ እየተጠቀመ አገሩን ከጠላት መንጋጋ አላቅቆ ለተተኪው ትውልድ ነጻነቱን ያጐናጸፈ ለመሆኑ በታሪክ መነጽር መመልከት ይቻላል ።

መቼም ሰው ሁል ጊዜ እንደ ከፋው አይኖርም ፣ ገጠ ሬው የሚደሰትበትና የሚዝናናበት ጊዜም ነበር ። እዝ መራውን ሰብስቦ በሚያርፍበት ወቅት ፣ በረኽም አቦሬ የዶሮ ዓይን የመሰለ ጠላውን እየተጐነጨ፣ ስለ ፍቅር ያለ ውን ስሜት ፡—

http://ethioliberty.wordpress.com/

« ሕልም አልሚ ነበር ያውም ሁሉት መንታ ፣
እንቺም እዚያው ፍቺው እኔም እዚህ ልፍታ።
እንዳልበላ ጾሚ እንዳልጾም ገድሌ ፣
እንዲህ ሆኜ ቀረው ባንቺ ተለክፌ »

ብሎ ሲያሰማ እዚያ ያለው ሁሉ በጣቅ ይፈንዳ ነበር ።

በተዘፈንበት ቤት ይለቀስበታል እንደሚባለው፣ ደስታና ሐዘን ተፈራራቂዎች እንደ መሆናቸው መጠን ፣ በለኩት የሰውን ልጅ ሲጉበኙ ይኖራሉ ። ገጠሬው ሕዝብ ሐዘኑ መሪር ከመሆኑ የተነሣ ፣ ዘመድ ወይም አውቂያ ሲሞት ፣ ሴቷ ያረቷን እየደቃች ፊቷን ስትነጭ ፣ ወንዱ ደግሞ እርር ዙምትር ብሎ ማንባሩን በመፍጀት ሰብዙ ጊዜ ያዝናል ፣ ኋላም ጠባም የሞተውን ዘመዱን እያነሣ፣ ...

« አለቃትሳለሁ አላለቅስ እንዴታ ፣
የራቢ መድኃኒት እናት ዓለም ጠፍታ »

በማለት ያንጉራጉራል ።

በሀገራችን እነዚህን የመሳሰሉ ደስታም ሆነ ሐዘን የሚገለጽባቸው ግጥሞችና ቁም ነገር አዘል ተረቶች ከገጠሩ ሕዝብ ጋር አብረው ከአባት ወደ ልጅ ቃል በቃል ሲተላለፉ ኑረዋል ፣ አሁንም አሉ ።

ፍቅርና ሐዘን ፣ ወንድና ሴት ፣ ልጅ አዋቂ አይልም ፣ ለሁሉም እኩል ነው ። የቤት ሠራተኛ ስትፈጭ ፣ ስት ወቅጥ ፣ ሲታበካ ፣ ፍቅረኛዋን እያነሣች በፍቅር ትወዛወዛ ለች ። እንዳንድ ጊዜም እንዝርት ከእጇዋ ሲወድቅባት የፍ ቅረኛዋን ስም ትጠራና ድንግጥ በማለት እንኳንም ሰው የለ ብላ ውዘዋዜዋን ትቀጥላለች ።

በመጨረሻም ፣ ይህችን ጽሑፍ ልሚያነብ ሁሉ ላስ ተነዝብ የምፈልገው ፣ በአራት የተለያዩ ርዕሶች የቀረቡ ግጥ

ሞች መሆናቸውን ... ላቸው እንዲታወቅልኝ ነው ።

አልፎ አልፎ የግጥሞቹ የቤት መምጮ ፣ በሆሄ ሳይመ ሳሰል ይታተና በተመሳሳይ የሆሄ ድምፅ ቤት ያመታል ። የዚህ ዓይነት የግጥም ስልት ድርም የተለመደ ስለነበር ስኬት አይደለም ።

አድማሱ ደስታ

http://ethioliberty.wordpress.com/

የፍቅር ግጥሞች

እዩት እዚያ ማዶ እንድ እግር ሽንብራ ፣
የኔው እያ ዕገሌ አዲሱ ሙሽራ ።
እንሙልኝ እንሙልኝ እንሙልኝ እደራ ፣
እስቲ ላንሣሣ ሁለቱን በተራ ፣
ወንድሙን ጨምሬ ከናትዮው ጋራ ።

እምብዛም አልከፉኝ ይስም አላሰኝ ፣
እንደ ኑቱ ስፍር በድርበቡ ነኝ ።

ወንዝ ተሻግሬ በገላጣው ወጣሁ ፣
እህል ያልቀመሰ ጥርስ አይቼ መጣሁ ።

ሁለት ልጆች አሉ ስማቸው ማን ማን ፣
እንዱ ሰምቶ መቻል እንዱ ሰው ማመን ።

ከእንግዲህስ ወዲያ ይቅር ሰው ማመን ፣
በፍጥነት ጥሩልኝ ያንን መቻልን ።

ትልቅ እንደ ወርካ ክባድ እንደ ዝሆን ፣
ከዚህ ሆኜ ላንሣሽ እችልሽ እንደሆን ።

ብችል እችላለሁ ባልችል አዘግግለሁ ፣
ካንቺ ተለይቼ ምን ሰው እሆናለሁ ።

እረ ቂሱ ቂሱ መምሬ መጠኔ ፣
ወዶ የሞተ ሰው አለው ወይ ዙኑኔ?

ወዶ የሞተ ሰው የለውም ዙኑኔ ፣
እስከዚህ ካሠጋሽ ይሁንብሽ በእኔ ።

እንደ ቦሩ [illegible]
ያለው በንጋፀሁ ያጣ ባይኑ በላሽ ።

አንጓቷ የሚመስለው ዙሪያ ጠምበለል ፣
እቧን ያብሎኛና ዓመት ላገልግል ።

ትመሚለሽ ብዙ ላይ በሩን ላይ በሩን ፣
ጎይኔ እንደ መቅረየስ መንጠረው ዴሩን ፣
የዋለብኝ እንዳል አይጣው ብድሩን ።

ላሊበላ ሳሚ ቅል ያንጠለጥላል ፣
የሸጋ ልጅ ከንፈር ዕድሜ ይቀጥላል ።

እንዳልበላ ጾሜ እንዳልጾም ገድፈ ፣
እንዲህ ሆኜ ቀረው ባንቺ ተለክፈ ።

ክፍ እንደ ኮርቻ ዝቅ እንደ ኩረት ፣
ከዚያ እቄጥረዋለሁ ያንቺን መለየት ።

ሰደጂልኝ መርፈ ሰባራም ቢሆን ፣
ይጣም እንደ ሌሊቱ ቀን እንዳልባንን ።

መውደድ ይህና ሰንብት እኔን ከንበል ያርገኝ ፣
እኔ እንግዲህ አልቀል ካልቀለሱ እትገኝ ።

ሀብታም ደጋ ሲናር ነፋሻ ሀገር ፣
ድሆን ብቻ ቆላ ምነው እግዚአብሔር ።

ያን ማዶ ተራራ እኔ አርሼዋለሁ ፣
ሎሚና ትርንጎ አብትዬበታለሁ ።

ትርንጎውን ሴባ ወስዶ ጨረሰው ፣
ወይኔን ይጋር ቀረሁ እኔ ደካማው ።

ሰገሌ ሰገሌ የሚለው እንጉጉ ፣
እንደ ሰንጋ በሬ የሚዋጋው ጡጉ ፣
አለ ብርቱ ነገር እያብጠም አባጉ ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

አልጋሽ የዝሆን ጥርስ መክናሽ ሽንብቆ ፣
ትዝታሽ ይመጣል ስንቱን ጋራ ዘልቆ ።

እረ ምን ዓይነት ናት የተልከሰከሰች ፣
ቅድም ባከሳቱ አሁን ባያኔ አሰፈች ።

የባቱላ አበባ በመሰለው ጥርስ ፣
አሁንም ቅድምም ይናገረኝ እሱ ።

የጥቁር መስኖ እሸት ሲበላ ደርሼ ፣
ሞቼላችሁ ነበር ለጠንቄ ደርሼ ።

ሰንተራ ንግ እንጂ አያበቅልም ቡን ፣
ፍትር ለመጨረስ ያልታደልኩትን ።

እደስ ነው ለንቡል ነው ቅርንፉድ ነው ሼታሽ ፣
የፈተኖው ባልሽ በምን ነገር ፈታሽ ።

ዓይኗማ ጥርሷማ መች ይበልጣል ከሰው ፣
እንጉድ ነው እንጂ ሐረግ የሚመስለው ።

የበጊቱ እጉባ መልሶ በግ አይሆን ፣
ምኑን ተናግሬ አስቀይሜሽ ይሆን ።

የምስር አውድማ ኮለል የፎከተው ፣
ይታኖሽል ጥርስሽ የተዘናከተው ።

ያስፈራል ይላሉ ዚጋወደምን ፣
ሲመላለስ ያድራል ልቤ ብቻውን ።

እንደ እዲስ አበባ እንደ ባቡር መንገድ ፣
ልቀመጥ ልነሣ ልቁም ልንጐራደድ ፣
ሰው አለ ሰው የለም አያሰኝም መውደድ ።

እስቲ ተነጋግሪን ልስማው ድምፅህን ፣
እለየው የለም ወይ የኔ መሆንህን ።

አራዳ መካከል ያቦካል ባርኔጣ ፣
ትችለኝ እንደሆን ከነጓዜ ልምጣ ።

ምነው ትለኛለህ ልጅ ገና ልጅ ገና ፣
ዶሮም ትበላለች አጥንቷ ሳይጠና ።

አረጀህ አረጀህ እሚልብኝ ማነው ፣
ዶሮም የሚወደድ ገብስማ ሲሆን ነው ።

እኔስ ብዙ ነበር ላይኔ ጐድፍ አውጪ ፣
እንዲህ ውሰሽ አድረሽ ነገር ልታመጪ ።

እኔስ ብዙ ነበር ለዘላለማችን ፣
ምን ጊዜ ብንጠጣው አለቀ ውኃችን ።

የንጪ ላም ወተት በነጩ ቡይቴ ፣
የቀይዋ ላም ወተት በቀዩ ቡይቴ ፣
የጥቁሯ ላም ወተት በጥቁሩ ብቴ ፣
ይሆን ያልፈታ ሰው አይደርስም ከፊቴ ።

የንጪም ላም ወተት ጥርስሽ በረዶው ነው ፣
የጥቁሯም ላም ወተት ዕራብሽ ከፍታው ነው ፣
የቀይዋም ላም ወተት ሳንቃው ደረትሽ ነው ፣
ፈታሁት እንቺ ልጅ ልንገርሽ ይኼው ነው ።

እባርሽ አድራ እግርግዳው ሥር ፣
በረዶው ሲፈላ ንብሩ ሲያንምር ።

ዓሻቅቤ ሳየው ጋራው ከለከለኝ ፣
አይኗ ጥርሷ መጣ ተልኳል መሰለኝ ።

የዘንድሮው ልቤ እኔ አላውቅለትም ፣
እንደ ጥቁር ድንጋይ ጉልት ይላል የትም ።

ልቤ ዳር አዳሪ እይገባ ከቤቱ ፣
የጅቡ ደግነት አለመባሉቱ ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

አዳኞች ወረዱ ምን አውሬ ተገኝቷል ፣
እንዳትሳሳቱ ልቤ ዳዋ ገብቷል ።
አርጌውን ሽማ እዛፍ ላይ ሰቅዬ ፣
እኔ መሞቴ ነው አዲስ አዲስ ብዬ ።
ቆንጂ ሚስት አግብቶ ለሰው ከማበደር ፣
መልክ መልካም ይዞ እንደ ጊዜው ማደር ።
ጉም እጅ አገር የለው፣ ይወጣል ተራራ ፣
እዚህ ቁሞ ብዬ ልቤ ከዬ ጋራ ።
ሆዴን ብዳብሰው አጣሁት ልቤን ፣
አንቺ ዘንድ መጥቶ እንደሁ በይ እዘያው ይሁን ።
እንሶስላ ሞቃ ስሚ ጨብጣለች ፣
ራቧን ተሠርታ ወሰባ አድርጋለች ፣
አሽከሮች ተንሡ ታጠቁ ትላለች ፣
ይህቺ ወይዘሮ ወዴት አስባለች ።
ወንቃ የጠጅታ ጉሊት ደባደቦ ፣
መውደድ ይገላል ወይ ደብድቦ ደብድቦ ።
ፍየል አተርትሮ ይመስላል ሠርገኛ ፣
እንዴት ነው ከንፈርሽ የጥርስሽ ዘበኛ ፣
እኔስ በቁንጮሽ ላይ ቢጋሜሽ ብተኛ ።
እሄድ እሄድና እላለሁ ታከተኝ ፣
መውደድ በጎራዴ እያነካከተኝ ።
በጎራዴም አይደል በጉዶ በጉዶ ፣
ልቤ እንቢ አለኝ እንጂ ጠይም አሽከር ወዶ ።
ጠይም አሽከርና ቤተስኪያን እንድ ነው ፣
እንዳልሳለመው ልቤ ምናምን ነው ።
ወዳንቺ ስመጣ ወደቀ በርኖሴ ፣
ማሪኝ እንታረት በሦስቱ ሥላሴ ።

በካሚዮኑ መንገድ በወለሊግው ፣
አንቺን ተከትዬ ይብላኝ እሞራው ።
እስቲ እንደ መኪናው ልሂድ በግንባሬ ፣
አገኝህ እንደሆን ከነገ ከዛሬ ።
የሄድህበት አገር ደብዛው ቢጠፋኝ ፣
መቀነቴን ሸፈው ቡና አፈላሁኝ ።
ቤትህና ቤቴ ሻጣ ለሻጣ ነው ፣
ድምጥህን አሰማኝ ነፍሴ ልትወጣ ነው ።
እንደ ዳንግሴ በግ ሳይሽ ደስ አያለኝ ፣
አዳኜም ገዳዬም አንቺ ነሽ መሰለኝ ።
እስቲ በጎፈሬሽ ሰግዩን ንኪው ፣
ካንቺ መለየቴን ቀሩጡን ልወቁው ።
ሄደች በላይ በላይ እንደ ቤት ከዳኝ ፣
ጥርሷን እያሳየች ልቧን ሳትሰጠኝ ።
አበባው አበበ ንቡ ገባልሽ ፣
እንግዲህ ያገር ልጅ ማር ትቢያለሽ ።
አገሯ ላይ ደጋ የምትበላው ገብስ ፣
የጠይም ሰው ገላ እንዲህ መለስለስ ።
በተስኪያን አልሰምም የሰው ደብር ብዙ ፣
አምና ወቂት ከፈልሁ ዓይኔ ዞሮ ባየ ።
አንቺ መልክ ባላገር ትዝታሽ ወይዘሮ ፣
ከደጅሽ ይገኛል ፍቅር ዞሮ ዞሮ ።
መልኬ ኩሳኩስ ነው እኔም አውቀዋለሁ ፣
ዐመሌ ኩሩ ነው ጀርጋዳ እወዳለሁ ።
ጥሩ እህል አለቀ ተራገፈ ቂቃው ፣
ምናምኑን ልብላ ሆራቴን ልተው ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

የታጠቀበቱ ክርትሙሲው ዱር ፣
ያሲያዛትም ጋሻ አምሳለ ጀምበር ፣
እሱ ቀውስ የለውም ጦም ውሎ ቢያድር ።

አግላጅ ሲበዛ ባለፅዳ እምቢ ሲል ፣
ተጨንቅሁ ተጠበብሁ ወዳጄን ናልኝ ስል ።

በፍቅር ጉዳና ቤቱን አሠራና ፣
ያባ ያጎል ጀግና ድንገት ይደርስና ፣
እንቺ እሽከር እንዴት ዋልሽ ብሎ ይለኝና ፣
ደፋ ቀና ብዬ እጅ እነሣውና ፣
ዘንጉን በቀኝ እጁ ጨበጥ ያደርግና ፣
እኔን በግራ እጁ ለቀም ያደርግና ፣
እንሂድ ይለኛል እትዝታው አዝ ፣
አሥርና ገንዞ እኔን በሱ ፍቅር ።

እፍን ሞንት ያለች የሽማ ድንኳን ፣
በነፋስ ልብ አልባ የበቅሎው እንዞር ፣
ውኃ በብርሌ ገሸር መኖር ፣
ከማይረባ ሰው ጋር ፍቅር መጀመር ፣
ተጨነቅሁ ተጠበብሁ ወዳጅህ በምር ፣
ተወኝ አያ እገሌ ይቅር ያ ነገር ።

ትመሟለሽ ብዬ ድንጋይ ስለቃትም ፣
ፍቅር ጣለሽ አሉ ያንቺ ጉድ አያልትም ።

ነጭ ወረቀት ማዛ ላንተም ይሻልሃል ፣
የሰው ልጄን እንከን ምነው ይጥልሃል ።

እሽከሩ አያ ገብሬ ባለ ምልኩት ፣
አይጠፋም አለቃ የትም ቢልኩት ።

ሽጋው አያ [illegible]
ቀማኛው ወገቡ ድጉን ጉረሰው ።

በደልዳላ ስፍራ ይተከላል ዱባ ፣
በቀጭን ሸማ ላይ ይደረባል ካባ ፣
እሽከር ነው ጉብል ነው ሚስትም እላገባ ፣
ሥጋዬን ጨርሶ ወደ ነፍሴ ገባ ።

ተሌሊት ጨረቃ ተቀን ጀንበር ነሺ ፣
ዶሮ መረቅ ከንፈር እንኮዩ ጥርስሽ ፣
የወደድሁሽ ጉብል ነሆለልሁልሽ ።

ፈቅ ብላ ተኝታ አላት አማርኛ ፣
የምትገድለውን ሰው አናውቀውም እኛ ።

ጠይም መልክ መልካም ፍጹም በውበቷ ፣
ካሮኋት ጀምሮ ልቤ ሆናለል ቤቷ ።

ውበቷን እንዳየሁ በመደሰት ፋንታ ፣
እዝን አተነገዝ ጀመር ልቤ እያመነታ ።

ምን አለበት አሁን ልቤ ልብ ቢገዛ ፣
እንዲህ ከምጉዳ አሳብ ከማበዛ ።

ለኔ አትሆንም እያልሁ ለኔ ላትሆን ስኛ ፣
ጥርጣሬ ገብቶኝ አጣሁ መተንፈሻ ።

ጠይቂ አልተረዳሁ ሐሳቢን አላውቀው ፣
በሚዳ ነው እኮ እኔ ምጨነቀው ።

አሁንም ቅድምም ትናገረኝ እሷ ፣
የባቄላ አበባ በሚመስለው ጥርሷ ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

ለግድግዳው ነው ወይ የምትቸገሪ ፣
ቁርጡልሻለሁ እንግዲህ ቤት ሥሪ ።

ሠብራትም አይብራ ድፍንፍን ይሁን ፣
የኔ ሆድ ጠይሜ ትመጣ እንደሆን ።

ዓይኗን ክፍት አድርጋ ስታደርገው ከድን ፣
መነሁሴ ከገዳም ጎሽ ይወጣል ከሆን ።

እኔ ምን ቸገረኝ አጥንቷ ባያጠራ ፣
ፍቅሯ እንደ ሙጀሌ እንጀት የሚበላ ።

ቀድሞ ነበር እንጂ በሰባራ መንገድ ፣
ፋቂ ደበናንሳ አያሰኝም መውደድ ።

የምታውቋት ሁሉ ንገሯት ትረዳ ፣
እሷን ፈልጌ ነው እንዲህ የምጮኻ ።

አልሰማች ይሆናል እንደምን ላስረዳት ፣
እንደራሴ አድርጌ እኔ እንደምወዳት ።

አሁን ምን ቸገራት ጭንቄን ተመልከታ ፣
ብታነጋግረኝ አጠገቤ መጥታ ።

ኮመሞቂ በፊት እንድ ቃል ልናገር ፣
ምንም ዘመድ የለኝ ከፍቅሬ በስተቀር ።

ልቤ ተሠውሮ ባሳብ ከምቀጣ ፣
መድኃኒቴ እሷ ናት ጠይሟ ልጅ ትምጣ ።

ተንገበገብሁ እኔ ነድጂ ነድጂ ፣
ልቤን የምትሠውር ጠይም ልጅ ወድጂ ።

በጣም የተዋበች ጠይም ዓሣ መሳይ ፣
በፍቅሯ እማሥራ ሥቃይ የምታሳይ ፣

ለተመለከታት ሁሉ ለዓይን ያማረች
ወደረኛም የላት ከሴቶች መካከል ።

ያች መልክ መልካም ጠይም ሴት ወይዘሮ ፣
ቀያይ ሴቶች ሞልተው ቀይ ዳማሞች ተርፈው ፣
እዩት ጠይሟ ልጅ ልቤን ስታክንፈው ።

እንደኔ ተንድፎ ጠይም የወደደ ፣
የልቤን ሁኔታ እይቶ በፈረደ ።

አንቺን አንቺን ብዬ አንቺን ካላገኘሁ ፣
የለት ሞቴን እንጂ ሌላም አልተመኘሁ ።

አገሩ ወዲያ ነው ጉም የጋረደው ፣
ወየው አኳኋኑን ትዳሩን ያየው ።

ዳዊቱን ዘርግቶ ፣ ድጓውን ዘርግቶ ከጮልበቱ ላይ ፣
ደብተራው ቢደግም ሰው አይገድልም ወይ ።
ሠላሳ ደብተራ አርባ ሊቃውንት ፣
ይህ ሁሉ በሙሉ ዘርግቶ ዳዊት ፣
የሰግው ሲያነት ያየው ሲታክት ፣
ይሀን እንዲያነበው መምህሩን ጥሩት ።

ሹሙ ተደነቁ መዝገቡን ቢያዩት ፣
እንተ እንዳልህ ብለው ሹመው ሰደዱት ።

የሰግዩ ኮከብ ወርዶ ዘብ እደረ ፣
ታማንብህ እንጂ መች ተመሰከረ ።

የሰግዩን ኮከብ ብቄጥር ሠላሳ ፣
መድኃኒት የለም ወይ እንተን የሚያስረሳ ።

በራሴም እንዳትሆኝ ሰንቡል ይነካሻል ፣
በእግሬም አንዳትሆኝ ሄዶ ያስሄድሻል ፣
ዓይኔም ላይ እንዳትሆኝ አይቶ ያሳይሻል ፣

http://ethioliberty.wordpress.com/

እሁንስ የለው ዘር ብንመካከረው ፣
ያንቺ መቀመጫ ከልቤ ውስጥ ነው ።

እኔ ተሳስቶኝ እጣን በላሁ ልጄ ፣
ከነምልክቱ ሣፍ አለ ከደጄ ፣
ኀወጣ ሲገባ የሚነካው በእጄ ።

ዋርሱን ጉራማይሌ የተጠቀረው ፣
ወገቡን ጎራዴ የወዘወዘው ፣
ሊገድለኝ ነው እንጂ መች ሊያድነኝ ነው ።

የዚህ ቤት ባለቤት በስንት በራ ያርሳል ፣
የተመለመለች ዋንቅሽ ልጅ አድርሷል ።

ንቢቱ እናታችን ሠራችው ተጨንቃ ፣
ከወይኑ ከግሩ ከጠጄ ፈልቃ ፣
እኔም እንድወደው እንዳፈቅረው እውቃ ።

እኔ እንዲህ አልቀርም ለፍልፌ ለፍልፌ ፣
እናገረዋለሁ እንግይ አልፌ ፣
ለቂስ ወልደ ማርያም ለመምራ ከንፌ ።

ሥጋዬም አለፈች ነፍሴም ተመናጎች ፣
የሕይወት መድኃኒት ካንቺ ላይ ተገኘች ።

ተረከዝሽ ሎሚ እሾህ ይወጋሻል ፣
እኔን ሚዳ አድርገሽ ብትሄጅ ይሻልሻል ።

አሩሲና ባሌ ጎን ለጎን ነው ፣
ፍቅርና ንንርን ትኩስ ትኩሱን ነው ፣
ከበረደ ወዲያ የእጣር ውኃ ነው ።

እነኳኩራሽ ስጪኝ ልብላው እንደ ማንም ፣
ፍቅርና ሙያ እንድ ላይ አይሆንም ።

እጉንብሶ ቢሄድ ሞኝ ነወይ በት ፣
ነገርን ካልተውት ጣል አያደረጉ ።

እንገቷን ብሰብሰው ዘለላ ዘለላ ፣
ሐሰት ይመስለሻል ሳላየ ሰው ማውጋት ።

ችጋር እብድ አይደለም ዘሱ ሰው አያንቅም ፣
ሰነፍን ካገኘ አያነቃንቅም ።

ዘመር በል ስንፍና ከላ ከመንገዱ ፣
ከሁለት ተቁርጪል የጠላቴ ክንዱ ።

በዚያ በበረሃው በሜካው መንገድ ፣
በጣም ያስደስታል ሜማ እርጎ ሲሄድ ።

እኔስ እሄዳለሁ እሞራ ገደል ፣
ሙሩ ባለ ሽቦ ፈረሱ መጋል ።

ላይ ላዩን እላፊ መንገድ ተጠያፊ ፣
የሐምሌ ገበሬ በሾተል ንራፊ ።

አለው አማርኛ አለው እብነት ፣
የጋሜው አጣጣል የልጄ ውበት ።

አይጠቅለልም ብር በቅጠል ፣
ደርሶ በሰው ገንዘብ ልብ መታጠል ።

አሀያ መሜኔን ማነው የነገረሽ ፣
ገና ስደለድል ስወድን የቀረሽ ።

መርፌ ቢደነድን አይሆንም ጎራዴ ፣
ለወረተኛ ሰው ተጨነቀ ሆዴ ።

አገርሽ ቅርብ አይደል በግር አይመቺ ፣
እንደ አባትሽ በሬ ወይና በዩኝ አንቺ ።

አንገቷ ዝንጉርጉር እንደ ዘላን በሬ ፣
ሞል ብሏል መንደሩ የት ሄዳለች ዛሬ ።

ዘፋፋ እንደ ግራር ከባድ እንደ ዝሆን ፣
እስኪ ላንግማሽ እችልሽ እንደሆን ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

ፈሰስ ያለው ደምሽ እንደ ፈዋሽ ጠበል ፣
የማትመጪ ከሆንሽ ቅሪ እንጂ ምን ልበል ።

እረ ታመምኩልሽ ደክከምኩልሽ ፣
ትናንትና ማታ የወጋኝ ጡትሽ ።

እንቺ የሁልጌ የሁሉ ስልም ፣
ወፍጮ እንኳን ይሰያል ግርድፍና ልም ።

የሰው ግዙ ሆኖ የሰው ግዙ መውደድ ፣
እሳት በገለባ እፍ ብሎ ማንደድ ።

ሌትም እንዳልመጣ ይበላኛል ጅቡ ፣
ቀንም እንዳልመጣ ያየኛል ሰው ሁሉ ፣
ወሰደኝ በፈሰስ እንደ ውኃ ሁሉ ።

የሚጸጽ ከበድ ትባላለች ለምለም ፣
የሚያራርቅ እንጂ የሚያቀርብ የለም ።

እረ የኔ እበባ የኔ ሰውነት ፣
መሄድሽ ነው እሱ ሳንጨዋወት ።

እረ እበባ እበባ እበባ ሁኝልኝ ፣
እነም እንድወድሽ ሰውም እንዲያወቅልኝ ።

በይ ቀዬው ጮብሌ እንደ ቀረው ይቅር ፣
የሸመት እህል ነው የሰቀቀን ፍትር ።

እንት ያገሬ ውኃ አረንጓዴ አትልበስ ፣
እጠግልሃለሁ በደሀና ብመለስ ።

በዘንድሮው ወራት በመራሙሬው ፣
እንቺን ይዞ ገደል አይገባም ወይ ሰው ።

በመኪናው መንገድ በተደለደለው ፣
እንተን ተኩትሎ ይሄዳል ያደለው ።

አራዳ ገበያ ወፋ መከራ ነው ፣
እሺ በይ ድግሚ መውደድ እዝመራ ነው ።

እኔ ምንቸገረኝ ነጋዴው ቢያታርፍ ፣
እዝመራዬ እንጂ ነሽ እስከ ወዲያው ድረስ ።

ወረቀት ቢልኩት እንደ ቃል አይሆን፣
እኔስ እንጂ መጥታሽ ብነግርሽ ሁሉን ።

እንኚ ከወንዝ ወዲያ እኔ ከወንዝ ወዲህ ፣
ቀረን ተለያየን ቀን አታውቂ እንግዲህ ።

ምድቤን ምድቤን ሽመሉን ሽመሉን ፣
እቄረቍርበት እረኛውን ልቤን ።

ጣቷ እያዩ እበባ ዘለግ ያለ ጥንቅሽ ፣
በዚህ በፈለጉ በርሻው ምን አመጣሽ ።

ያንን ማዶ ጋራ አሳርሰዋለሁ ፣
ቋሚና ትርንጎ አስተክለዋለሁ ።

እንግዲህ ጀመረኝ ሆዴ ጤና ሲያጣ ፣
ያንን ጠይም እሽክር አስኪትሉ መጣ ።

ከጠይምም ጠይም ወዛም እወዳለሁ ፣
ለዚያ ለተማሪ እሞትለታለሁ ።

የደብተራ ወዳጅ ቢቀር ምናባቱ ፣
ጎራዴ ሲመዘዝ ይላል ባዛኝቱ ።

እንኳን ባዛኝቱ ይበል በሥላሴ ፣
እኔ እመደዋለሁ እስክትወጣ ነፍሴ ።

እጮተራው ጓሮ አረግ የለበሰው ፣
አንበሳው ከበላው የተልከሰከሰው ፣
አደባባይ ወጥቶ ጥንድ እሚመልሰው ፣
በዋርዳ ሳሙና ሚዳ እሚጨርሰው ፣
አባ ኩስትር በላይ አዬ ሰው አዬ ሰው ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

ማለዳ ማለዳ የሚፈላው ቡን ፣
ለሱሰኛ እይደለም ለሚአብከነክን ።
አብከንካኝ ይለኛል አብከንካኝስ እሱ ፣
የሚአብከነክነኝ ባይጋና በጥርሱ ።

ባይጋና በጥርሱ የነደለ ማነው ፣
የኔ ትዝታዎ ያው ልማደኛው ነው ።

እባክሽ እናቴ እፍኝ ሙሉ ገብስ ፣
ማር እልበላም አለ የሸኔው ፈረስ ።

መልክት የላከ ሰው በቅሎ እይልክም ወይ ፣
ይቸ የባላገር ልጅ ተብዬ ነው ወይ ።

እኔስ ተወው ልሁን የባላገር ልጅ ፣
እንዴት በግሬ ልምጣ የሸጌ ወዳጅ ።

እሸከራቱ ትንሽ ሳቆላ ክምር ፣
ልቤን ወሰድ ወሰድ ታደርገው ጀመር ።

ሽንበቆ ቢረዝም እላዩ ላይ ቃላ ፣
ወጣት ያገሬ ልጅ ዓይን ቀበዝባዛ ።

ቅዳሜ ገበያ ወድቄ ብነግ ፣
መቀነቴ ሁሉ ቅርንፉድ እነግ ።

ቅዳሜ ገበያ ትዳምን ያድርገኝ ፣
እንኳን የወይዴት የጠሉት ሰው ሲገኝ ።

እስክ ዶሮ ጩኼት ነበር ጊትነቴ ፣
ሰበክ ሴሊቴ መጣ ድህነቴ ።

ያቺን ደካማ ላም ቢወስድብህ ሴባ ፣
ያን ደካማ በሬ ቢወስድብህ ሴባ ፣
እንተም ድሃ ሁነህ ድሀ እንድታገባ ።

ባልሽን ያዥው እንጂ እንጂው እራስሺ ፣
እኔግ ከቤቴ የት ልሂድልሺ ።

ይሆንን የሴት ባል ስፈራው ስጠላው ፣
እንዲያው እምቢ ብሎ እረፈብኝ ጥላው ።

ተወንዝ ወዲያ ማዶ ተክያለሁ ሎሚ ፣
ቀይ ቀዩ ለኔ ነው እትሽተዳደሚ ።

ለምኔ ቀይ ቀዩ ዋጋ የበላውን ፣
መርጬ እነሣለሁ ጠይም ሎጋውን ።

እንጂ ደህና ደህና እኔ ነኝ ቀቢጥ ፣
ትናፍቂኛለሽ ወር ሳልቀሙጥ ።

ከቅጠሉ ሁሉ ግራዋ ለምለም ነው ፣
ትመጣለህ ብዬ መንገዱን አላምነው ።

ያንን ጥበብ ኩታ ፣ ያንን ጥበብ ቀሚስ የለበሰው የለም ፣
ትበልጣለች እሱ ያቺ ልጅ በቀለም ።

እድርኚኝ ሳም ሳም ከንፈራም ይደንድን ፣
መቼም ካዋሻኪው ከሰባቂው ላልድን ።

በል ብላ ፣ በል ብላ ፣ ብላ ገደለችኝ ፣
እቢ እየበረዳት እኔን ደረበችኝ ።

እንግዲህ ጀመረኝ ፍርሻ ፍርሻ ይለኝ ፣
አሰግየቴ ነው እቢን የሚሻለኝ ።

የታባሽ እንች ቡዳ እኔም እወቅሁብሽ ፣
ወይ ከሱ ወይ ከኔ እይሆንም ወይ ልብሽ ።

እያሜወተችኝ እያሜወትኋት ፣
ያመቱን ጉዳና ባንድ ቀን ሄድሁት ።

ወደድሁ እይል የለም ሁሉም በየቤቱ ፣
አለቃው ከኔ ነው ባለ ኑጋሬቱ ።

እረ እንዴት ያለ ነው መውደድ የሚሉት ፣
የለውም እጅ እግር እኔስ ያየሁት ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

እበድሁ እበድሁና እንግዲህ ልጨምት ፣
አንተም ጋሻ ጣዛ እኔም ኩል ልሸምት ።

ዓይንህን ባይኔ ላይ ጥለኸው ቢሰበር ፣
አውን በማን ዳኛ ትከፈለኝ ነበር ።

አውን በማን ዳኛ አውን በማን ዋስ ፣
ዓይንህን ባይኔ ላይ ጥለኸው ቢፈርስ ።

ጉልት ብዬ አድራለሁ ምድጃ ስሞር ፣
ላይን ከበልባሳ ለጠይም አሞር ።

ጉልት ብዬ አድራለሁ ምድጃ ታቅፈ ፣
ላይን ከበልባሳ ለጠይም አልፈ ።

የሚበቃ ጠጕሯ ላንድ አልጋ ጕዝጓዝ ፣
እንደት በጣ እጄ ሰው ይዛባል ጋዝ ።

ሲጫወቱ ማማር ሲሥቁ መድመቅ ፣
እንዲህ ያለ ሽጋ አይቼም አላውቅ ።

ማቅልኝ ሽጋ ልጅ ማቅ ባንተ ይደምቃል ፣
የላይኛው ጥርስህ በሐር ገመድ ታጥቋል ።

እቅፍ አርጎ ላመኝ ጉርጉሮ አርጎ ዋጠኝ ፣
እሱስ ለብልሃቱ ልቤን ሊያናውጠኝ ።

እኔ መሄዴ ነው ብርቱ ሥራ አሰብኝ ፣
ግንብ አስገንባለሁ ፍቅር ተንዶብኝ ።

አንት የገደል በቅሎ እርካብህ ያልጠና ፣
ወይ ትረሳኛለህ ሰው መሆን አለና ።

የተኳሽን ወዳጅ ተኳሽ አይነካትም ፣
የመንደር አውዳልዳይ ካገኘ አይተዋትም ።

ወይ ስጠኝ ቀለቤን ወይ አሰናብተኝ ፣
የጀግናውን ወዳጅ እያሉ ፈሩኝ ።

አንተ የጌታ ልጅ ሽማ አንጥፉ ባይ ፣
አንተ የጌታ ልጅ በቅሎ ሜኑ ባይ ፣
እኔ የድሃ ልጅ ያራሚ ጕልዳይ ፣
ሞንቅ ያለ ፍቅር እችላለሁ ወይ ።

እኔስ እሄዳለሁ አገሩን ጥየው ፣
እያዩ ማስተኛት ግራ ነገር ነው ።

እሄዳለሁ እኔስ እሄዳለሁ ፈራሁ ፣
ጌታው እረገዙኝ በሆዳቸው ቀረሁ ።

አይሸፈሽም በርበሬ በእንስራ ፣
ፍቅር ለማያውቀው አይመስለውም ሥራ ።

አይንተከተክም በርበሬ በመዳይ ፣
ፍቅር ለማያውቀው አይመስለውም ጉዳይ ።

ይወቀጣል እንጂ በርበሬ አይታሽም ፣
እመጣለሁ ብሎ ትልት ሰው አይዋሽም ።

እመጣለሁ ብሎ የቀረ ሰው አለ ፣
እኔም በፈንታዬ እምቢ ብል ምናለ ።

ትመጣለህ ብዬ ሳይ በሩን ሳይ በሩን ፣
እትህ የናትህ ልጅ እትጣው ብድሩን ።

አሻቅቤ ስሄድ ላብ እያጠለቀኝ ፣
ቁልቁለቱን ስወርድ እንባዬ እየነቀኝ ፣
መቅረትስ እትቀርም እስከዚያው ጨነቀኝ ።

ስሄድ በጨለማ ስመለስ በምሽት ፣
እንዲህ ይርባል ወይ የጥቁር ገብስ እሸት ።

ስሄድ በጨለማ እያናወዘኝ ፣
እዚችው ልተኛ መቼም ቤት የለኝ ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

ኩሽሽላው ቤቴ እያለ ኮሸሸ ፣
ያለኝ ይመስለኛል እንዴት እመሸሸ ።

ወየው ባደረገኝ የደጅሀን ሰርዶ ፣
እህያህ በበላኝ ጉራርዶ ጉራርዶ ።

ወየው ባደረገኝ ዝንብና ትንኝ ፣
ከንፈርህ ላይ ሆኜ እሽ እንድትለኝ ።

እኔ ወዲህ ማዶ ከብት እጠብቃለሁ ፣
ወገል ይዘሽ እንደሁ ማረኝ ይሻለሁ ።

አፋፉ ላይ ሆኜ ጩሽቴን ብለቀው ፣
መጣች ከነሊጥዋ ሳትሊቃለቀው ።

እንቺ ወዲያ ማዶ እኔ ወዲህ ማዶ ፣
እንገናኝም ወይ ገደሉ ተንዶ ።

ገደሉማ ሲናድ ይጫነን የለም ወይ ፣
እንዲያው በደፈናው እንገናኝም ወይ ።

እረ በሉ በሉ እረ በሉ ዛሬ ፣
ነገማ ሥራ ነው ይጠመዳል በሬ ።

ያሥራ አምስት ፍሪዳ ደም የረጋብሽ ፣
ቆሎ ነይ ጉብሌ ሰው ተጉዳብሽ ።

የበረቦር መንገድ አይችልም እግርሽ ፣
መቼም የኔ ዕዳ ነሽ ነይ ልሸክምሽ ።

እኔስ ብዙሽ ነበር ካይኔ ጉድፍ አውጪ ፣
እንዲህ ወደ ማታ ነዝር ልታመጪ ።

ሥጋ ስደጂልኝ ባዲሱ አገልግል ፣
ልብ አልበላም እኔ እንቺን ይመስል ።

የሥጋ መልከኛ የለም ወይ ከቤትሽ ፣
ታናሽና ታላቅ ያለ መለየትሽ ።

እይበላም እንጂ የኑግ እሸት እየው ፣
ለኔም እዘኑልኝ ሳፈቅራት ተለየው ።

ከሎሚ ላይ ጠርሙስ ፣ ከጠርሙስ ላይ ባላ ፣
ከባላ ላይ ጉታ ፣ ከጉታ ላይ ሳንቃ ፣
ከሳንቃ ላይ ሽጉጥ ፣ ከሽጉጥ ላይ መንቀል ፣
ከመንቀል ላይ ድንበር ፣ ከድንበር ላይ ሲደር ፣
ከሲደር ላይ በረድ ፣ ከበረድ ላይ ኩስኩስት ፣
ከኩስኩስት ላይ ኮከብ ፣ ከኮከብ ላይ ዘንዶ ፣
ከዘንዶ ላይ ሚዳ ፣ ከሚዳ ላይ ቅል ፣
ከቅሉ ላይ ሐር ፣ ከሐሩ ላይ ጨዛ ፣ ከጨዛው ላይ ብር ፣
ይሀንን የፈታ ከኔ ጋር ይደር ።

ይሀን የምፈታ እኔ አለሁ መሰሪ ፣
ታስታዋቂኝ እንደሁ መልካም መልካም ሰሪ ።

ሎሚው ተረከዝሽ ፣ ጠርሙሱ ባትሽ ነው ፣
ባላውም ጭንሽ ነው ፣ ጉታውም ሆድሽ ፣
ሳንቃው ደረትሽ ነው ፣ ሽጉጡም ጡትሽ ፣
መንቀል እንገትሽ ነው ፣ ድንበሩ አገጭሽ ፣
ሲደር ከንፈርሽ ነው ፣ በረዶው ጥርስሽ ፣
ኩስኩሱቱ አፍንጫሽ ነው ፣ ኮከቡም ዓይንሽ ፣
ዘንዶው ቅንድብሽ ነው ፣ ሚዳው ግንባርሽ
ቅሉም ራስሽ ነው ፣ ጨዛውም ወገብሽ ፣ ሐሩም ጠጕርሽ ፣
ብሩም ሳዱላሽ ነው ፣
ይሀንን ፈታሁኝ ደጅሽ ማደሬ ነው ።

እረ ቅሪ ቅሪ ይሻለኛል ፣
አገሬ ቄላ ነው ንዳድ ይገድለኛል ።

እሻቅበሽ ምጂው ሰማዩን በእምቧይ ፣
አብር ያደገ ሰው ባል አይሆንም ወይ ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

አምላው በጦር ያልቃል አምላው በንዳድ ፣
ሁሉንም ያስሄዳል ገራም ነው መንገድ ።

እዩት እዚያ ማዶ ዛፍ ይወዛወዛል ፣
ያ ነሁላላ ባልሽ ቆሞ ያናውዛል ።

ቀዪቱ ጊደሬ ምኑን ነው የምትወጂው ፣
በሰው በረት ገብተሽ ልቤን እታንድጂው ።

በሄድሽበት ሁሉ ፍቅር ስመሞን ፣
በትንሽ ሙቀጫ ይወቀጣል ቡን ፣
እሷ ጅማ ነባች እኔ እንዴት ልሁን ።

ውኃ እንኳን ይሄዳል ልቡ ባስበው ፣
እንዴት አሳድጎ መልምሎ ለሰው ።

ዝንጅሮ በገደል ጦጣ በዛፍ ላይ ፣
ሲጫወት ይውላል የልቡን ጉዳይ ።

የሸማኔ ልጅ ናት ጥበብን አልባሽ ፣
ጥርቢ ሰው ይገላል ከንፈሯ ሲሸሽ ።

ዝንጅሮ በገደል ይላል ባኩም ጀሌ ፣
የጥርቢ ጥቁራት ያስለውጣል ዋሌ ።

የኔ አዝመራ ስንዴ ያንተ ዘንጋላ ነው ፣
አንተ ቁርጠህ ስትሄድ እኔ አልሰብረው ምነው ።

አንተስ ቁረጠልህ ስለት ነው መሰለኝ ፣
እገዘግዛለሁ እኔን እምቢ ብሎኝ ።

ተጉድጓዳ ስፍራ ይበቅላል ሞኩኝ ፣
የሱም ዓይኑ ጠፋ በእም ጣለብኝ ።

እዚህ ተቀመጪ እዚያ የታየሽኝ ፣
ስንቁን ጋራ ዞሮ ይመጣል ብለሽኝ ።

የአዛምራ ቅጠል ፍየል አይበላውም ፣
አንጋሬ አንጋሬውን መውደድ አይገባውም ።

የዝንጅሮ ቁርበት አይሆንም መጫኛ ፣
ጨነቀኝ ጠበበኝ ያንቺው መገናኛ ።

ወዳንቺ ስመጣ ምነው መመለሴ ፣
አይደለሽ መሐረብ አልይዝሽ በኪሴ ።

የሰጉን እንቁላል ሠላሳ ስምንት ፣
ከምወዳት አሽከር ወንድሜ ይሙት ።

ከምትወደው አሽከር ወንድሟን ስጠላ ፣
የእም እቴ ትሙት ልጅዋን አስከትላ ።

ያንተ ልብ እዚያ ላይ እኔም ኩሩ ልጅ ነኝ ፣
ወጥ አታውቂም ብለህ ስታንገዋልለኝ ።

እዩት እዚያ ማዶ ዐመሉ ጥሉት ፣
ባይን የታየው ሁሉ ይበላ መስሉት ።

ምድር አለስለሶ አራሽ የዘራሽ ፣
አንቺ የመስኖ እሸት ምርቅ ያልበላብሽ ።

ከጉማ ላንት ላይ በቅለሽ እንደ ሞፈር ፣
ረሃብሽ ጠናብኝ ስትይ አፈር አፈር ።

በቀይ ዶረቷ ላይ ጥቁር ባደርግባት ፣
ሐር ማተብ መስሎ እንዴት አማረባት ።

አንቺ የመስኖ እሸት ያብራጅ እየር መላይ ፣
የሕሙማን ሕይወት ባይን በጎ ገዳይ ፣
እኔ እናትሽን ብሆን ለሰውም አላሳይ ።

ከምስራት የመጣው የነፋስ ወገቦ ፣
አይምታው መልክሽን አንቺን መሳይ ዣንቦ ።

የቆላ ነጭ ጤፍ ደምብል አደይ ባቷ ፣
እግር ተረከዟ የሠራ አከላቷ ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

ጉብሉ እኔና እንቺ የሠራነው ቤት ፣
ዳር ዳሩ ቆርቆሮ ግሕሱ ገኑት ።

በጀጠባቡ ላይ ኮት የደረገመው ፣
ልቤን እንደ ቆሎ አሽቶ ቄረጠመው ፣
የሠራ አከላቱን እንደ ንብ ወረረው ።

ሄደች በካሚወል በማይከሰሰው ፣
ሄደች በሩብላ በማይደረሰው ፣
እስቲ ቁጭ ብዬ እንባዬን ላፍስሰው ።

በድንጋይ ላይ ድንጋይ ደራርበው ቢተኙ ፣
መች ይቄረጭራል የልብን ካገኙ ።

ከመዋፎ ጋር ውሎ ከመበላሸት ፣
ይሻላል መት ሆኖ ተቀብሮ መቅረት ።

እስቲ ልነግና ልየው ጨረቃውን ፣
ልቤ ሽጋ ወዶ ያጮህል ዕቃውን ።

እንዲህ ያለ ነገር ለወግ ያልተመቸ ፣
ትናናትኝ ጀመር አብሬያት ተኝቼ ።

ቀጣፊ ነህ አሉኝ የነበያ ቁና ፣
እኔም ቆሎ ተወሀህ ሕመሜ ሳይጠና ።

ሳይህ ደስ ይለኛል እንደ ቀይ ዶሮ ፣
አጥፊዬም አልሚዬም እንተ ነህ ዘንድሮ ።

እስላም ደሽ ሄዶ ፣ቂስ አይበላም የዝን ፣
አጣሁ የልብ ወዳጅ ብመገዝን ባስመዝን ።

አልተፈሰፈለም እንቁላሉ ገማ ፣
በጣም ያሳዝናል ሰው ወዳጁን ሲያማ ።

ከቅጠሉ ሁሉ ዱባ ነው ሰፋፊ ፣
እንተ ሁሉን ደራሽ እኔ ተጠያፊ ።

ማናም እይደለም ወይ ያንቺማ ነገር ፣
ሲቁ ተረከዝሽ የደብር መምሀር ፣
ቡችሎች ጡቶችሽ እነናት እይምር ፣
ቀለብ አሰሬሉ ነውና ጥቁር ።

ይህ አውራው ወገቢ ግርማው የሚያበር ፣
ሆር ዞሮ ቢያየኝ ገባው መቃብር ።

ትናንትና ምቹ ዛሬ ተቀብሬ ፣
ድምፅሽን ካልሰማሁ እኔ አልውልም ዛሬ ።

ለበን ተገድግዶ በመውዜር ሲማገር ፣
እኔ እከፍለዋለሁ ባንች የመጣን ነገር ።

ግይንሽ ወራሪ ነው ቅንድብሽ ደጀን ፣
ፈረስኛው ጥርስሽ ማረከኝ እኔን ።

ግይንሽ ጉላ ጉላ የትንባሆ ፍሬ ፣
እንቺን የወለዱ መልካም ሽማግሌ ።
የልጅ ወዳጅና የሽንብራ እሸት ፣
ቢበሉት ቢበሉት ጠብ አይል አንጀት ።

እቱ በጎፈሬሽ ባንዲቱ ዘለላ ፣
እጆህ ወጋኝ ብለሽ ቅሪ ወደ ኋላ ።

እጆህ ወጋኝ ብዬ ብቀር ወደ ኋላ ፣
ሰዉ ምቀኛ ነው ያደርገዋል ሌላ ።

እኔ ላንተ ብዬ ስከላ ሰንጣ ፣
ክሶ ታያት አሉኝ ሰው ነገር አያጣ ።

አቀበት ቁልቁለት አይችልም ጉልበቴ ፣
እጥርሶችህ መሓል ይሠራልኝ ቤቴ ።

እራበኝ እራቡ ጎኔን ጎኔ ወጋው ፣
እንቺ አለሽኝ ብዬ ሳልሸምት በበጋው ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

እንተ ሁሉን ደራሽ እኔ እርባ ጦመኛ ፣
ይሀን በመልሀን ፈት በነገርኽኛ ።

እንደ መጀመሪያው መጨረሻው ቢያምር ፣
ባንተ አይጮይል እንጂ እኔ ምንም አልል ።

አልናገርኽም ምን አባቴን ብዬ ፣
እንዲያው ማታለሌን መለመኔን ጥዬ ።

ሕልም አልሜ ነበር ለምን ነገርሁሽ ፣
እንዳትፈጂው ሳውቀው እንዳይሆንልሺ ።

እንኳን ይመወዜ አሥራ እምስቱ ጨው ፣
ትቀሪያለሽ አንቺ የምወድሽ ሰው ።

የሄድሽበት ሀገር እየታየኝ ዛፉ ፣
አልጠጋም አለኝ ጎኔ ከምንጣፉ ።

ኑግ እራት አይሆንም እስከ እንጎት ቢበሉት ፣
ውሽማ ባል አይሆን ምን ቢያቆላምጡት ።

ቁልቁለት ቁልቁለት ይወግራል በቅሎሽ ፣
ልቤ ተፈናጢል ትጥይዋለሽ ።

እግራታ ሆኖ ይታያል እምባዬ ፣
ዓይል ገባሁልሽ ሁለት ዓይኔ እያየ ።

በበላልኝና እንጂቲን ባራሰው ፣
የማይገኝ ሽጋ ለምን ይመኛል ሰው ።

ውኃው ተንቄርጵራ ዓለምም ቀሪ ነው ፣
የጨለማ መንገድ የወር እይጋ ነው ፣
ከልብሽ ምከሪ ዘመድ ምቀኛ ነው ።

ይህ ፍቅር የሚሉት ብዙ ነው ዐመሉ ፣
እያቅበጠበጠ ሰው ያስጠላል አሉ ።

ዐረመኔው ልቤ ዐረመኔ ወዶ ፣
እንደ ገደል ዐፈር አለቀ ተንዶ ።

አባይን በዋና ሙጋን በያረቴ ፣
እንዴት አርን ሳመኝ ንገሪኝ በሞቴ ።

እትፍ አርን ሳመኝ ብዬ ብነግርህ ፣
እንኳን ጥርስህ ሊሥት ያራል አንጀትህ ።

እንዲህ ቅርብ ነው ወይ ጉጃም በሚታታ ፣
እንደ ነፍሰ ገዳይ የምትመጪው ማታ ።

የፍቅርን ምንነት ለማወቅ ብትሻ ፣
የትዳር ዓደኛ አብጅ ኪሐበሻ ።

ያቺን ጠይም አሽከር ልቤ እንዲየ ሲወዳት ፣
ትናንት የዘነበው ተራሰው ወሰዳት ።

አሸር ባሸር በልቶ ሆዴን ከማለት ፣
ጦም ውሉ ጦም አድሮ ቪጋን መሸመት ።

እንጨት ሊታቅሚ ብትን ወደ ዓር ፣
ጉና ምሳ ልኝ ነኝ አላሙትም ቀጠር ።

መዲያ ማዶ ሆና ብትንልጠው ይረቷን ፣
እኔስ መስሎኝ ነበር እሳት ፈጀው ቤቷን ።

ጉበዝ ሆ እያለ ሠርገኛው ሲያቅራራ ፣
ፍሪዳው ተዋሎ ቢሰጥ ላንሜሞራ ፣
አንቺ ጉና ልጅ ነሽ እልም ያልሽ ኩታራ ።

ከምቧይ ካብ ሳልወጣ ጉና በልጅነት ፣
ሰትምህርት ደረስች ብለው እንዶግለት ፣
አሁን ደስ ይበለን ሳንሞት እንዳራት ፣
በግለት ዕድሌን ሰባብረው አስቀሩት ።

አይከፉሽ የኔ እኅት ተዪው እጅሩሩ ፣
ባንቀልባ እንዳላዝልሽ ከባድ ነው ነገሩ ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

በዚያ በሜጫላ ቤት እንተን ያየሁህ ለት ፣
እስቤ ነበረ በርሬ ለሙጥፋት ።

ሳንሞት እንዳራት ብለው በመያቹ ፣
ከትዳር አሸክላ ቀረሁኝ ገብቹ ።

አድሬ መቁርቁዝ ዘወትር መቁርቁዝ ፣
የምበላው እህል እየሆነ ንቀዝ ።

መልሶ ቢበላኝ እየመነመነኝ ፣
የልጅ እናት ሁኜ ኩስጨ ቀረሁኝ ።

አይክፋን አይክፋን አይክፋን እኖን ፣
ዕድሜ መስታወት ነው ብዙ እናያለን ።

ልውጣ ሶማ ደጋ ልመለስ አገሬ ፣
ለማትሆነኝ አሸክር ምነው መቸገሬ ።

ለማትሆነኝ አሸክር ለማታዋጣኝ ፣
እንካ በሽታህን ጢናዬን ስጠኝ ።

እንባው ላይ አድሬ ከጉብታው ሥር ፣
አሞራው ሲያረኝ ጅቡ ሲያጓምር ፣
የቃልቻ ልጅ ነው እያውትም ፍቅር ።

የቃልቻ ልጅ ነው የሶላ ታጣቂ ፣
የገበሬ ልጅ ነው የሞፈር አራቂ ፣
የወታደር ልጅ ነው የዘናር ታጣቂ ፣
ታምሚእለሁና ሂዱልኝ ታዋቂ ።

ታዋቂ ሂዳችሁ ምን አሉ ምን አሉ ፣
ሠላሳ ወረቀት አስጥፉላት አሉ ።

ሠላሳ ወረቀት ምንድን ነው ዓይነቱ ፣
ክክብ ቄጣሪዎች እስቲ መላ ምቱ ፣
እያዩ መናፈቅ ምንድነው ብልሃቱ ።

አሻቅቤ ባየሁ ቁጥር ፈለጉኝ ፣
አንተን ባይሮብላን ወሰዱህ መሰለኝ ።

እረኛም ጀንበቆ ባሕር ያጠለቀው ፣
ትንፋሹ እንደ አረቂ የሚሰረንቀው ፣
ዘላን የንብ አውራ ጢስ የነቀንቀው ።

ውስድ ትዝታህን ይሆን አቦዛኝ ፣
የማስቀምጥበት ዐታም አላገኘ ።

እኔ እየወደድኳት እሷ እየጠላችኝ ፣
ዛሬስ ብላ ብላ ንግግር ነግችኝ ።

ክቄረጠችብኝ ግፍቀሬን ከውርደት ፣
እባካችሁ ሰዎች አንጋገረው በሏት ።

ገራገሩ ልቤ ደንዳና ልብ ወዶ ፣
እንደ ገደል ወፈር አለቀ ተንዶ ።

ፍቅር እታውት እሷ ምን ብዬ ልንገራት ፣
እንኳን ላፈቀረ ገና ከሩቅ ላያት ፣
ልብ ታቄስላለች በትዝታ ጥይት ፣
መልሶ ግዳንስ ግነው ያስተግራት ።

እንቺ የወይን ሐረግ እቱ ቀዛቢይቱ ፣
ቀዘባ ቀዘባ የግር እሸቲቱ ።

ገና ያልባለቀች ሊጋዋ ወጣት ፣
መሳይ ከንፈርቹ የጉመራ እሸት ።

ምነው ባያረገኝ ወንድሞችሽን ፣
እንዳንጋግርሽ አብሬሽ ብሆን ።

ጉንጪን ተደግፋ ስትጫወት ላያት ፣
ያፍንጫ እወራረድ የጥርሷ ንቅሳት ።
ከዋክብት ዓይናቹ እንዚያ ብርሃናት ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

ሰረት አርገው ሲያዩት የባይንዋን ብልጭታ ፣
ተከሰው ይቀራሉ የልብ ትርታ ።

ምነው ባደረገኝ እቴ እንዳትሽን ፡
ተሸክሜ እንድኖር የደም ገንቦሽን ።

ያንቺን የደም ገንቦ ተሸክሜ ባድር ፡
ስኔ ይሰጠኛል ይስታና ፍቅር ።

ምነው ባደረገኝ ውብ ቀሚስሽን ፡
ምነው ባደረገኝ አሸንክታብሽን ፡
ምነው ባደረገኝ አልቦ ድሪሽን ፡
ሽጌ ካንቺ ጋራ አብሬ እንድሆን ።

የሣር ክዳን ቤቱ አዲሷ ጎጆዬ ፡
ገመና ከታቹ ጥላ ከለላዬ ፡
የመናር ትርጓሜ ይዞተር መግቢያዬ ፡
አንቺ ነሽ ጎጆዬ ጋሻ መከታዬ ።

ከዳተቱ ግርጌ ከወርካው ባሻገር ፡
ከለምለሙ ሜዳ ጭው ካለው መንደር ፡
ተከባ ሁሪያዋን በሰንበሌጡ ማር ፡
ታየችኝ ጎጆዬ የትዳሬ ምስጢር ።

በጠኖት ወጥቼ ስመለስ በምሽት ፡
ልጆች ሲጨፍሩ እያሉ የኔ እባት ፡
ውዴ ባለቤቴ እሷም ደስ ብሏት ፡
ትቀበለኛለች በደስታ ብዛት ።

ካትክልቶች መካከል ያለሽ ጽጌረዳ ፡
መንፈስ ታድሻለሽ ለሚያይሽ ማለዳ ።

በየቀትሩም ያው ነሽ ክነልምላሚሽ ፡
በሩት ያውደኛል ናርዶሱ መዐዛሽ ።

ለምለሙ ቅጠልሽ ለዓይን ያስጠማ ፡
ንቦች በቀሰሙት እሱን እዘውትረው ፡
ነጩ ቀይ አበባሽ ፈክቶ የሚታየው ፡
የኔን ልብ አቅሰሎ ሚወጋው ሰምን ነው ።

እንቺ ጽጌረዳ ፡ የኔ ጽጌረዳ ፡ የውበት ልምላሜ ፡
የቀይ ግምጃ ቀለም የኔ ጽጌረዳ ፡ የሕይወት ፍጻሜ ፡
መዐዛዬ ሕይወቴ ጮልበቴ ድካሜ ፡
በእውኔ እያየሁሽ ትመጫለሽ በልሜ ።

የደም ገንቦ ውበት ጽጌረዳ አበባ ፡
ትጥፍጥፍ አድርጌ ይገርሽ እቤት ልግባ ።
ከመከዳዬ ላይ ከቤቴ ላኑርሽ ፡
እንዳትጠወልጊ እንዳይጠፋ ሽታሽ ።

ጀርጋዳ አንተ የኔ ጀርጋዳ ፡
ሳይህ ደስ ይለኛል ታጥቀህ በግለዳ ፡
ጀርጋዳ እወዳለሁ እንዳንተ ያለ ሎጋ ።

አድጸመ መልካም እንከን አይወጣልህ ፡
የጥንትሽ አገዳ ውኃ ዳር የበቀልክ ።

ጮብል ሰመመኔ ሽታዬ የኔ ዓለም ፡
እኔስ ካንተ ሌላ የማፈቅረው የለም ።

እህል አይበላኝ አንተን እንተን ሳስብ ፡
አካል የኔ አበባ ብት በል የኔ ዓለም ።

በጣም ይጨንቀኛል ስትጠፋ ከፊቴ ፡
እየተሰራጩህ በሠራ አከላቴ ።

እኔ አንተን ማፍቀሬ ለወግ ለትዳር ፡
ፈቃድህ እንዲሆን አብረን ብንኖር ።

ይኽ ነው ምኞቴ አካል የኔ ሽጋ ፡
ተሳስበን በፍቅር እንተኛ ዛንድ አልጋ ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

እምራ ተኳሰላ ሙሽራት ዓይናማ ፣
አቤት ማስደሰቷ በሠርጓ ዋዜማ ።

ባደኞጀ ሁሉ እያሉ ሙሽራት ሙሽራት ሙሽራት ፣
ባሸንክታብ ድሪ በልባልባ ቀሚስ እንዲት አሳመሯት ።

እናቷም አባቷም ቤተሰብ በሙሉ በጣም ደስ አላቸው ፣
ተንቄጥቁጣ ሲያዩዋት ሙሽራት ልጃቸው ።

እንዲህ ነው ጋብቻ እንዲህ ነው ትዳር ፣
ከሙሽራት ጋራ ሙሽራው ሲያምር ።

ይችን የመሰለች ቀዘባ ልጅ ሉጋ ፣
እንዴት አገኘሃት በስንት ፍሊጋ ።

እንኳን አስጊጠዋት አሳምረዋት ፣
እንዲያው ተፈጥሮዋ የደም ገንቦ ናት ።

ተጎሙ ሆ በሉ አበባ ጣሉባት ፣
መሄዷ ነው እኮ ሙሽራትን ሽኟት ።

እናቷም አባቷም መርቋት ሳሟት ፣
መልካም ዘር ጋብቻ እንዲሆንላት ።

እጎት ወንድሞቿ ይታይ እንገታችሁ ፣
ለባዕድ ይዘፍናል እንኳን ለጎታችሁ ።

ልዩ ትዝታ አለው ሠርግ የሠርግ ሊታ ፣
ሙሽራት ትደሰት እስክታው ይመታ ።

ክፍል ሁለት

የሐዘን ግጥሞች

ሲያሥሩት ሲገንዙት ሙቷ እያፈሰሰ ፣
እንኳንስ የሰማ ያየ አለቀሰ ።

ሲጋጀው ወላጎላው ለኛ ምናችን ነው ፣
እንዳንዘቀዘቅ መጠጊያው ወዴት ነው ።

ንጉሡን ፈርቼ ሞጣ ሰድጀት ፣
የለቅሶ ሆነችኝ የዝና ያልኳት ።

በላይ ትለፍ እንጂ በላይ ተጠንቅቃ ፣
የዝና ጌታውን ወይ ሟቃ ወይ ሟቃ ።

በበቅሎ ሰጥተውኝ ብመልሳት ባልጋ ፣
ዘመድ የላትም ወይ እኔን የሚወጋ ።

ይጨነቃል እንጂ ያባት ሆድ ላመሉ ፣
ይጨነቃል እንጂ የናት ሆድ ላመሉ ፣
ልጅሽ እወንዝ ወርዶ ኸያ ሆኗል አሉ ።

አውን ማን አለና ውብ እንደ ጋማስ ፣
እንደዚህ ይውላል ካባና በርናስ ።

ተዋት አትትበሯት ጣሏት ተመንገዱ ፣
የማናት ሙሽራ እያሏት ይሂዱ ።

መልኪ ጠወለገ ብለሽ የላክሽብኝ ፣
ጥርሶቹ ረገፉ ብለሽ የላክሽብኝ ፣
ዓይኖቹ ሟሸሹ ብለሽ የላክሽብኝ ፣
እኔ መምጣት እንጂ ሌላ ምን አለብኝ ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

እንዲህ በጠለንጂ ወድቃችሁ ወድቃችሁ ፣
እምን ሾካሾክ እውሬ መጣላችሁ ፣
የምፈርሰው እኔ እንዳልጠብቃችሁ ።

ዛፉ ወደቀና ግግቱ ተንጫጫ ፣
እንግዲህ አይገኝ የልጅ ዕዳ ዋንጫ ።

በሬዎች ተጽቁር ገበሬው ደንቆሮ ፣
አይናንርም ወይ ዘር አለቀ ብሎ ።

ከኔና ከናንተ ማን ይሻላል ይሆን ፣
የኔስ ያሳዝናል የልጅ አልባ መሆን ።

እዩት ያላያችሁ የኔውግ ፍሬ ፣
ያለ ጊዜ አፍርቶ አረገፈ ዛሬ ።

አበባዩ አልቅጪ ምን ሆነሽ ትኖሪ ፣
ከእንግዲህ ወለቀ ያባ ኳሣ ሰሪ ።

የዛሬውን እንባ ለራሴ ላልቅሰው ፣
ዓይኔ እየባከነ ጅብ የሚበላኝ ሰው ፣
ዘላለም ንበረ ለሁሉ የሚያርሰው ።

ያ ዓንዱ የማነው ተሰትሎ ከማገር ፣
ያ ጀንጥ የማነው ተሰቅሎ ከማገር ፣
ልውርዳችሁ እምጡት ጌታውን ይናገር ።

ማነው የቁረጠው የመንገዱን ሾላ ፣
አላፊው አግዳሚው ቀላውው እንዳይበላ ።

ዘውቻ ሆነ አሱ ተነገረ አዋጅ ፣
ወንዶችስ አለቁ ሴቱ እንሂድ እንጂ ።

ዘንድሮስ እግዚአብሔር ከጦርነት አዳህ ፣
መልካም መልካም ጉበዝ ትመለምላለህ ።

የወንዶግግ ጀግና ተገለጠ ዛሬ ፣
ንግዚአብሔር ነው እንጂ ሰው እንዲህ አደዚንም ።

ዓንዱ ብትል ዓንዱ አልገዛም ወይ እኔ ፣
ሽንተ ብትል ሽንተ አልገዛም ወይ እኔ ፣
የሰሌን ቶብ አርገህ የጀድከው ምናኔ ።

እገተ የኔ ወንድ ና ቁም ከኋላዩ ፣
የሽመል አጥራ አደችሁም ገላዩ ።

አ አዳም መሬት እንተ ብሎ ሲያዩራጅ ፣
ሞት አይነጥንም ግለት ነበር እንጂ ።

ወትርም ልግዱ ነው የኛ ቤት ጉምሳላ ፣
አበባ ነው እንጂ ፍሬው አይፀላ ።

እረ ግረኝ ግረኝ ግረኝ ተጉንብሼ ፣
እግዚአብሔር ይማርህ ሳልልህ ደርሼ ።

ወየው ሲባል ውሉ ወየው ሲባል ሙሾ ፣
እንደ በከረ ሰው እንደ ተበላሸ ።

አላድጋኝ ነበር እንዲ ጌሾ ፍል ፣
አላድጎኝ ነበር እንደ ባርቁፍ ፍል ፣
ወሰደብኝ እንጂ ብድሬን ላልከፍል ።

እንዴት ያሉ ናቸው አንጨል ተናጋሪ ፣
አውን ማን አለና ከናት ኳሳት ኗሪ ።

አባት የሌላችው እንሂድ ምናኔ ፣
አባት የሚመራ ብናነኝ ጀግኔ ።

እኔን ከንበል ያርገኝ ከንበሴ ከንበል ፣
አይንጣም ወድቆ ጀግናና ብርሌ ።

የት አለ ጉብዝናው የትእል ወንድነቱ ፣
በከር አይደለም ወይ የታመረው ጫቱ ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

አለቅስልሃለሁ አንተን እያድርገኝ ፣
ከሞልሁኝ ካደርሁኝ ሞቱ ካልቀደመኝ ።

ገሳ እንኳን የለውም እናቀብለው ፣
ያገን መሳይ ጉበዝ ዝናሙ መታው ።

የአበባዬ ወንድም መንገዱ በደጄ ፣
ቅቤ በልቻለሁ ወተት ጠጥቻለሁ ሳይታሠር እጄ ።

ዘላለም ተመስገን አበባ ነበረ ፣
ለኔ ሳያድለኝ ሳያፈራ ቀረ ።

እናቴ አልሻለሁ ስምሽን አሳገጬ ፣
ዘጠኝ ወር ካምስት ቀን ሥጋሽን ለብጬ ።

አወጣ ስል ወረድሁ መንገድ አሳስቶኝ ፣
እስቲ ልመላለስ ምንም ቢታክተኝ ።

የት ልደረስ የሱ ልጅ በጓላ ቀርቼ ፣
መላቂያ ሆንኳቸው ሰባሳጋሮቼ ።

እኔም ወንድም አግኝ ጠምጀ ነበረ ፣
የዚህ ዓለም ክብረት ተጀምሮ ቀረ ።

እንደ ሾላው ቅጠል እንደ ብላናው ፣
እርግፍ እርግፍ አለ ጀግና ሰው ምንው ።

ግርያም ሞተች አሉ ግርያም የትኛዪቱ ፣
እናት ትሆናለች ጭንቅ እግላጅቱ ።

ሰሉን ሳላስገሣ መታብር ላልለምን ፣
እናቲን ቀብሬሽ ዓለምን ዓለምን ።

እንኳን በሠላሳ ቢታረስ በመቶ ፣
እናት የሚያበቅል ምን ምድር ተገኝቶ ።

እናቴ ወዳጄ እልሻለሁ ልጅሽ ፣
አሁን ካፈር በቀር ምን ይዘሻል በጅሽ ።

ከቅጠሎች መሐል ያች ቅጠል ምንድናት ፣
ስሟን አሳንሳ ወይንናት ወይ እናት ።

አላውቅህም ያልሽኝ እንደ ዘመናይ ፣
እንጀራ አባቴ ቤት አልነበርህም ወይ ።

እናንት ዘመዶቼ በጣም እትቸኮሉ ፣
ጣይቱ በተሮታ ትደርሳለች አሉ ።

ምነው ወነኖቼ አሉ ምድር ምድር ፣
ሲርበኝ እንዳልበላ ሲመሽ እንዳላደር ።

የኔ ዘመዶችስ እንድ ጥፋት አላቸው ፣
ምነው አይነሡ መሬት ከነካቸው ።

ምድር ያለ በራ እዝር ያለ ወንድም ፣
ያም ቀን ነው እንጂ ይቀራል የግድም ።

ወንድም የሌለው ሰው ከጢፍ ፍሬ ያንሳል ፣
ከፉ ሲናገሩት ቀና ይመልሳል ።

መልካም ሳያልቅብኝ ተናግሬ ክፉ ፣
ባፌ ጠፍቼአለሁ ባፋችሁ አትኮፉ ።

እንደ ሰማይ ኮከብ እርቃኝ እናቴ ፣
ያም አልወጣም እንጂ ተወግቷል እንጀቴ ።

ነፍስ እግሯን ተሰብራ ወድቃ ተኝታለች ከቤተ ነነት ፣
ፍሪዳ ረዱላት ሙክት ረዱላት
በከንቱ ነው እንጂ ሥጋ ላያድናት ።

አለትሳለሁ እንጂ ምነው አለማንባቴ ፣
እንደ ሰማይ ኮከብ ስትርቀኝ እናቴ ።

እንጀራም በላሁኝ ወተትም ጠጣሁኝ ፣
ዛሬ እናቴን ባጣ እንዴት ተሳቀቅሁኝ ።

በሠላሳ ድንጋይ በሜን ዐፈር ንብታ ፣
እናት እናት ቢሏት እናት የት ተገኘታ ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

እናትም ያሳችው አባትም ያሳችው ፣
ሰኞ ተሜውቱ ሥራ እየፈታችው ፣
ወደ ኋላ ጸጸት እንዳይመጣባቸው ።

በክንቱ ነው እንጂ እንዳያው መለፍለፌ ፣
ከዳኖ ቢዋሰት ይገኛል ወይ መርፌ ።

መራቷ ብረሪ ብረሪ ብረሪ ፣
እናት ሞተች ብለሽ ሄደሽ ተናገሪ ።

እጉትም ከባሏ ወንድምም ከሚስቱ ፣
እናቴ ነፍልኝ ዕዳ ከታችቱ ።

እንዲህ ለሚቀረው ለሚፈታው ነገር ፣
ከናቷ ልጅ ጋራ ብዙ መነጋገር ።

ውኃ በቅል ይገር ልከተልሽ ወይ ፣
ምናልባት ከመንገድ ብትገላገይ ።

ውኃ ብለሽ ነበር እገኝሽ ወይ አጣሽ ፣
ገንዘብ ጉም ቆራጭ ነው ከደሙ በጠጣሽ ።

ወይ እኔን አትጠራኝ ወይ እጉት አትመለስ ፣
አሁን የናፈቅኸኝ እስከመቼ ድረስ ።

ባላንጦችህ ሁሉ እንዲት ደስ አላቸው ፣
እኛ እንበሰብስም እንሞትም መስሎአቸው ።

እባክህ ክፋኑ እባክህ ገናገሮ ክፉኛ አትሠራት ፣
ልቧ መቼ አሰበ ሞት እንደሚጠራት ።

ምስጥና በመሚት ተማልተው ባንገትሽ ፣
ወሬር ዳኛ ሆኖ ቆማል ከደረትሽ ።

እስቲ ጠይቁልኝ ወንዙን ሳትሻገር ፣
ለማን አደራ አለች ያንድ ልጅዋን ነገር ።

ረፃቡ ከሆዴ ወረዶ አበቀለ ፣
እናት ዓለም ብትኖር ትንቅለው ነበረ ።

በመልክሽ አትጣጫ ሩፍንጫሽ አውራጃ ፣
በቀለበት አሉ እንዶድና ሙጃ ።

አንበሳ ወረዶ አፋፍ አፋፉን ፣
ተንግ እባት ዓለም አሲዘው በሩን ።

ሌት የበላ ዳኛ ቀን የጣለ እንዳንሆን ፣
ኑልኝ ወንድሞቼ ያለ እናንተም አይሆን ።

ቢመታኝ በድንጋይ መታሁት በኩበት ፣
ወነን የሌለው ሰው የለውም እንደበት ።

እንገራግረኝ እንጂ ደርሰህ እንዴት ትመታኝ ፣
አንተ ሰው ቢኖርህ የኔን ሞት ቢፈታኝ ።

የናት አገር ቀሚስ ያባት አገር ሸማ ፣
ነጠላ አይደለም ወይ የሰው አገርማ ።

ያ መልካሙ ጣትሽ ቅቤ የሚያበጀው ጠላ የሚያበጀው ፣
አለ ሀምትር ሀምትር እሳት እንደ ፈጀው ።

ላንቺ ይብላኝ እንጂ ልጅሽ ያድጋል በእጁ ፣
እንደ ጉታ ፍራሽ ወድቆ በየደጁ ።

አልመሰድህም ብላ ታገናሰች መካን ፣
አያት ወላዲቱ አይኗ ሲባክን ።

የመካን ምን አሳት ያለ መቀንታ ፣
ቀብረው ሲመለሱ ይወረራል ቤታ ።

እንዲህ ይሞቃል ወይ የሰሌን ቀሚስ ፣
እንዲህ ይመቻል ወይ የድንጋይ ትራስ ፣
ልጇን አላሰችም እስካሁን ድረስ ።

እናንጫዬን ጠላ ምነው ሸተተው ፣
እቤት ማስጠንሰሌን ማረጌን ስተው ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

በሽታ የወጋው አልዳነም እንጂቴ ፣
ሳለቅትሰውና ልሂድ ወደ ቤቴ ።

እቴ መስታወትሽ ወድቆ ተሰበረ ፣
መተያየትማ ለኔም ላንቺም ቀረ ።

ዓይንሽ ይታየኛል መልክሽ ይታየኛል ፣
እንደ ነበር አርጎ ማን ያወራልኛል ።

አባትህ አያውቀኝ እናትህ አታውቀኝ ወገንህ ኤያውቀኝ ፣
አለቅትሳለሁ ዘመድ ሲናፍቀኝ ።

ዐርብ ዕርብ ዕረፈኝ ዐርብ ዕርብ ዕረፈኝ ፣
እናቴ ነበረች የምታስነፈፈኝ ።

አብልተሽ ፣ አጕርሰሽ ፣ አልቅስልኝ ያልሽኝ ፣
እንዲያውስ ሲከፋኝ የት ይደርስ ብለሽኝ ።

እንደ ዘላን አውራ የምታናድሰው ፣
እንደ ዳልጋ እንበሳ ግርማዋ የሚያስፈራው ፣
ምን ወንድ ይፈሪና እጅ እግሯን አሠረው ።

ቪ ብረት ከኋላው ቪ ብረት ከፊቴ ፣
ያስከትል ነበረ በሕግንቱ ፣
እጁ ታሠረና ብጆውን አደረ ከመቃብር ቤቱ ።

ጠበንጀህም ሰሰው አገርህም ለሰው ፣
እገሣሀ ባላንጣ የልቡን ያድረሰው ።

ጉሮም እናቲቱ አላንድ አልወለዱ ፣
ያ አንዱ ሞቱ አሱ ያ አንዱ ያ ወንዱ ።

ውኃ በቅል ይገር ሳላስታዋብዎ ፣
ፍትፍት እንደ ያዘ ታሠረ ጣትዎ ።

አስቲ ወየው ልበል ቆሚ እንደ ልማዴ ፣
ተሰብስቦ ሄዷል ያ ሁሉ ዘመዴ ።

የማነው አዳራሽ ያናኛል ተኳሾ ፣
ጌታውን የጣለ አያውቅም ወይ ባዶ ።

ቀጭን አመልማሎ ካገልግልሽ ላይ ፣
እመይቴ ወይዘሮ እትፈትልም ወይ ።

የኔማ ወንድሞች ወደቁ በተራ ፣
የኔማ እኅቶች ወደቁ በተራ ፣
ብቻዬን ቀርቼ ሳሳብ ለመኩራ ።

እናንቅ የኔ ሰዎች አልቃችሁ አልቃችሁ ፣
እኔን ዕዳ ከፋይ አርጋችሁ ሄዳችሁ ።

ምነው እኔ በሞትሁ ድሃው ወንድምሽ ፣
የምትሰጪበት የምታበዪበት ከሚፈርስ ቤትሽ ።

እኔስ አውቀዋለሁ ከሰማዩ ደጅ ፣
አንተ አድሮ እንግዳ ሞት ፣ሰው አጥፊ ነህ እንጂ ።

እናልትስ ካላችሁ እናልትስ በጀሻ ፣
በጀማናዥ ቀሚስ በጀማናዥ ጋሻ ።

እነዚያ በበሉ ፣ እነዚያ በገዙ ፣ እነዚያ በነዱ ፣
እኔን ዕዳ ከፋይ አድርገውኝ ሄዱ ።

አላኩራህ አለኝ ከንዱን ብንተራሰው ፣
እንዴት አንድ መጠጊያ ከቤቱ ያጣል ሰው ።

ከንፍ ያለው እሞራ አይወድቅም ከዛፉ ፣
እኔን አሰወገን ምን አናግሮኝ ከሱ ።

ጉባጣ ነህ አሉኝ ጉባጣ ነኝ ወይ ፣
ከሰው አልጣላም ጀርባዬን ሳላይ ።

እገርዎ ይጋ ነው አያስቀምጥ ብርዱ ፣
ቋሚ እንኳ የለም ጌታ ምን ያንዱ ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

ጠፋብህ አላሉኝ ከቃቤት ሸማው ፣
እናቴን እናቴን እንዴት ተጉዳሁ ።

አገርም ሜዳ መስክ የለበት ተራራ ፣
ዱጨ ውኜ ስማው ስኩት ሰው ሲጠራ ።

በሽተኛው ሁሉ ይሰን ጊዜ ሙት ፣
አባት ከመሰመን ውትት ከማለት ።

እንደ ኮረሪማ እንደ ውትት ዛፍ ፣
እናት ይሸተኛል በመንገዱ ላልፍ ።

እበላለሁ ብዬ እጠጣለሁ ብዬ ሆዴ እንዲያ ሲማማ ፣
የኔስ ዘመዶቼ ሆኑ አሉኝ አፈሳ ።

ደሙ ወርዶ ወርዶ ድንጋዩን ገደበው ፣
ያለ ፍትሐ ነገሥት የተደበደበው ።

እናት የሌለው ልጅ ፣ አባት የሌለው ልጅ የገደል ላይ ሣር፣
ማሩም አይታጨድ ልጁም አይዳር ።

ጀግና ነው ይላሉ ተኳሽ ነው ይላሉ የታል ጀግንነቱ ፣
በክር አይደለም ወይ የታሰረ ጣቱ ።

አባቱ በበቅሎ ልጅዮው በፈረስ ፣
ይቀዳደማሉ እኔ እፈርስ እኔ እፈርስ ።

ምንኛ ክፉ ነው እፍ የነካው ነገር ፣
ስሞት ታሳቅሻለሽ ብሎ አጉሮሶኝ ነበር ።

እንዝርቷ በውጥን ስፈቷ በውጥን ፣
እኔ እንዳልቁርጥላት እንደርሷ አላፈጥን ።

ከሁሉ ከሁሉ የልጅ ሞት ይብሳል ፣
አለ ካራ መትሮ አለ አባት ይጠብሳል ።

ሞትማ ሞትማ አባትም ይሞታል ይታዘናል በጣም ፣
አገሩ ነውና ልጅ ከሆድ አይወጣም ።

ዘወር ዘወር ብላ አየችው ቀሚሷን ፣
እረሳችውና ባፈር መለወሷን ።

እዚያ ላይ ያለች ሸክላ ሠሪ ፣
ድሃ ናት እሱ ጦም አዳሪ ፣
ማን በነገራት ጥበቡን ፣
ሰው ዐፈር መሆኑን ።

ሲርበው ማብላቱን ሲበርደው ማልበሱን ይተውና ዘመድ፣
ሲሞት ወየው ወየው ይመስለኛል ማበድ ።

ሞትማ ይሞታል በየሁላው ያጅ ፣
እንደ ወጣች ቀረች መባልዋ ነው እንጂ ።

እናትሽ አረረች አርራ እንደ ቅጠል ፣
ላይሆንላት ቀረች ዕድሜ መቀጠል ።

መች ዐፈር ይሄዳል ተውኖ በፈረስ ፣
ሰው ይሄዳል እንጂ እመውደቂዮው ድረስ ።

ዐፈር እበድርዋት በቱና ሰፍራችሁ ፣
አገሯ ስትገባ ትመልስላችሁ ።

ውኃ ትበል እንጂ እህል ትበል እንጂ ፣
ተደፍታ ተገኘች በጉሮፉ መሄጃ ።

ከጠፉ ባድማ ጠለንጅ ከወረሰው ፣
እንዴት ተፈልጎ ይገኛል እንድ ሰው ።

መቀበሩስ ይሁን ዳኛ ካለ ካገር ፣
እኔስ የጨነቀኝ ያስታማሚው ነገር ።

እኔን ሰው እኔን ሰው እኔን ሰው አያርገኝ ፣
አንድዜ ከጠፉ ተፈልጎ አይገኝ ።

ሞት ተመላለሰ መንገድ አደረገኝ ፣
ከእንግዲህ ቢመጣ ካለኔም አያገኝ ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

ባለቅሰው ባለቅሰው ዓይኔ መነመነ ፥
እንዲሁ ብተወው ዓለም ሐዘን ሆነ ።

ሰው ከሞተ ወዲያ ከወረደ አንጋዳ ፥
ወዳጁን አይጠቅም ጠላቱን አይጉዳ ።

እንደ መራት ሆዳም እንደ ሞት አጥዳይ ፥
ልጅን አላድን ዓለሙን ላያይ ።

የቅጠል እንጀራ ያፈር ጠላ አርገሽ ፥
የገና ዕለትማ ትጠረኛለሽ ።

የእናት አስታማሚ እያለች ከቤቱ ፥
የአጎት አስታማሚ እያለች ከቤቱ ፥
ጕርፍ የበላው ገደል መስሎ ሄደ አንጀቱ ።

ባለቅሰው ባለቅሰው ዓይኔ ሆነ ወንፊት ፥
ምነው ሞቼ ቢሆን ከሰዎቹ በፈጣ ።

የናት ሦስት ዓመት ቢታዘንላት ፥
የአባት ሁለት ዓመት ቢታዘንለት ፥
የወንድም አንድ ዓመት ይህንም ሲበዛ ፥
ምሽቱ ታለቅሳለች ወገናጅን ይዛ ።

እስቲ ወየው ልበል ሁሉት አለኝ መርዶ ፥
የትንሽ ልጅ እራብ የበሃታ ባዶ ።

ጉንፋን አይነካቸው ቋቁት አይነካቸው ፥
የዚህን ቤት ልጆች የወጊ አለባቸው ።

እስቲ ወየው ልበል የወየው ገበሬ ፥
እናትና አባቴን በእንድ ቀን ቀብሬ ።

ኧያ ምን ያለ ነው የተነለፈለፈ ፥
እንደ እደይ እበባ ማልዶ የረገፈ ።

መታመን ነው እንጂ የሰው ቁም ነገሩ ፥
ሞትማ ጭብሩ ነው ለሰው ልጅ በዘሩ ።

መጀ ታመመና መቼ ሆነ ሞቱ ፥
እግዚአብሔር ይማርህ ላይል ጕረቤቱ ።

ቁም ነገር ነው እንጂ የሰው ልጅ ዘመዱ ፥
መች ይሸኖል ወዳጅ እርቀው ሲሄዱ ።

ሰው የማያውቅ ሰው ክፉ ሰው ተፈጥሮ ፥
ስሙን ሞት የሚሉት የማይሰጥ ቀጠሮ ፥
ሰው ነው ያልነውን ሰው ፥ ወሰደው ዘንድሮ።

እረ ሰው እረ ሰው እረ ሰው በውነቱ ፥
ሞት በሰው ሲጫወት ዝም ብሎ ማየቱ ።

መቼም አይረሳ የልጅነት ነገር ፥
ትዝ አለህ መሰለኝ የምትፈጨው ወፈር ።

ታማቢ ሰው አጥታ ሀብቷን ከወረሰው ።
እንዴት ተፈልጎ ይገኛል አንድ ሰው ።

እግዜር ሠርቶ ሠርቶ ትንሽ ሲቀረው ፥
ታቦት ሁሉተኛ በናራት ምነው ።

አሞራና ዶሮ አይ እኛና ሞት ፥
ሲመጣ መንጫጫት ቄይቶ መርሳት ።

ሥጋ አልኳችሁ እንጂ ሥጋ ጉማ ጉማ ፥
መች አጣሁ አልኳችሁ የተመቀረማ ።

እኔስ እሄዳለሁ አባይ ተሻግሬ ፥
እናቴ ከሞተች ምን አለኝ አገሬ ።

ወንድም እንዴት አለህ በቀስተ ደመና ፥
የምድር ዓለምስ አይገኝምና ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

ከሞት ጋር የዋለ ሞት የመከረው ሰው ፣
መቼም ቤት አይሠራ ምን ጊዜም ቤት የለው ።

እባክህ አዳምጠኝ እንድ ቃል ላውራልህ ፣
ወዴት ትሄዳለህ ትዳርህን አፍርሰህ ።

አንተ በዚህ ዓለም መናር ከጠላህ ፣
እንግዲህ ዘመሚት ይሁን ዘመድህ ።

ለኔ ይብላኝ እንጂ መመከያ ላጣሁት ፣
አንተማ ገብተሃል ከዘላለሙ ቤት ።

ሰውነቴ ከሳ አለቀ ሥጋዬ ፣
መች ይደርሳል ይሆን የጽዋ ፈንታዬ ።

የእንባ ደም ሲፈስ ከመቃብርህ ላይ ፣
ከፈንሆን ፈተህ መለስ አትልም ወይ ።

ምን ያደርግልኛል ወርቅ ጕትቻሽ ፣
ምን ያደርግልኛል ወርቁ ቀለበትሽ ፣
ፈትፍቶ የሚያጕርሰኝ ባልታሠረ ጣትሽ ።

ያ ጕምላላ ሽጋ ያምር የነበረ ሲወጣ ከቤቱ ፣
እኔን ከምበል ያርገኝ ዐፈር ሆኖ ሲሄድ አላየች እናቱ ።

ያች ጠጕረ ሙና ሴት ምነው ባትሞት ፣
እዩ ስታበላ ስታፈተፍት ።

አስቤ ነበረ እንጅን ልቀድምሽ ፣
ምነው ቶሎ ራቅሽኝ በጣም ቸኩለሽ ።

እኔ ልደፋልህ እኔ ልከንቸር ፣
ተሰካበት ጥይት በገዛው ዝናር ።

በየጦርነቱ ስትባል አጅሬ ፣
በየደባባዩ ስትባል አጅሬ ፣
እጅ እግርህ ታሠረ እንደ አንድ ሰው ዛሬ ።

እንተ አለኝኝ ብዬ ስመካ ስመካ ፣
አወይ የሰው ነገር ሞኑህ ነወይ ለካ ።

የሚያጀረጅረው አውራው ከበረቱ ፣
ምን ያደርግልኛል ካለባለቤቱ ፣
ረግረግ ረግረግ አለ ሊውጠኝ መሬቱ ፣
ባይኔ ተመልከቼ በጂ ያፈስሁቱ ።

ቶሎ ቶሎ ሄደህ ተመለስ በሰኔ ፣
አለ በሰላህን የሚለው ያም ለኔ ።

ቀን የደረሰውን እያጋጠማት ፣
እሷን ባለ ጋሻ ገዳይ አረባት ።

አያ ሞት እንግዳ እንዲያ ሲያናዝዝህ ፣
ማንን ማንን ጠራህ ከእንያ ዘመዶችህ ።

እናንተ ወደኛ አትጠረጠሩም ፣
እኛ ወደ እናንተ ምን ቢሆን እንቀርም ።

ዝናብም አትዝነብ ቤቱም አታፍስ ፣
እባት ዓለም ሆዴ እንዳይበሰብስ ።

አረ እናንተ ሆዬ ከብት ተወደደ ፣
የትናንቱ ጕብል በአሞር በቅሎ ሄደ ።

አባት ያለውና አባት የሌለው ፣
ሲሄድ ያስታውቃል ዋግ እንደ መታው ።

እንዳላስቃቅስ ማላ ነበረብኝ ፣
እንዲያው እነባለሁ እንደ ፈረደብኝ ።

ግራዋ ግራዋ የሚመረውን ፣
ማማሻ እደረኳት እቴ ድግሜን ።

ያይንሽ ሽፋፍቱ ያንገትሽ አውራጃ ፣
አብቅሎ ይከርማል እደይና ሙጃ ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

ግፍና በደል መግለጫ ግጥሞች

ድብልቅልቅ ድብልቅልቅ ያልሽው ቀን ቶሎ ና ፣
ምስጥና ምስለኔ ሰውን ፈጅቷልና ።

ያውሬ ትንሽቱ ያች ሞጨሞላይቱ ፣
ገደላ ትሄዳለች ጭር ሲል መሬቱ ።

ተጉዘን ተጉዘን እንደ ጀፌ እሞራ ፣
ወይ መሬት እይሰጡን ወይ እርስን እንበላ ።

አልቤኑ ደም ለምዶ ቢልጅጉ ደም ለምዶ ፣
እንደ ላም እረኛ ይሰማራል ግልዶ ።

ሲሆን ተከናነብ ያለዚያ ልበስው ፣
ፊቱን ዞር እያውትም ከኩራ ወዲያ ሰው ።

ክዱር አውሬ ሁሉ አሳማ ነው ሆዳም ፣
ወዳጁን እይጠቅም ጠላቱን አይጉዳም ።

ሱሪዬን አውል ቂ እገልድሚያት—አለሁ ።
ቀን ያገኘሁኝ እንደሁ እታጠቃታለሁ ።

ግይጨው ከበረሃው የተጣለው ጠጅ ፣
ለፈሪም አይበጀው ለደፋር ነው እንጂ ።

ክቶ ምን ሊሆን ነው ፈሪ ማጦንጦኑ ፣
ቅጠል እይበጠስ ካልደረሰ ቀኑ ።

ሀንተም ተው እንተም ተው የሚል ጻኛ ጠፍቶ ፣
አራውን አረያው ከቀንበሩ ፈትቶ ።

ጠጉሯ ገሰገሰ ይሆነው ቸገፈ ፣
ቀድሞ ባልተሠራች ይሻላት ነበረ ።

አያችውላት ወይ የጠጉሯን መከራ ፣
ትላንት ተቋረጠች ደግማም እትሠራ ።

ወረቀት ጣፈሽን ባገኘው ልክሰሰው ፣
ያን ቀለምሽን ነው ዐፈር ያለበሰው ።

ሚስቱስ ታገባለች የማይሞት ሰው ቢገኝ ፣
እኔ ለሰውዬው እናቱን እያርገኝ ።

ምድርን ተጠንቅቂ ቀስ ብዬ እረግጣለሁ ፣
ነገ ከርስዋ በታች መሆኔን አውታለሁ ።

ወንድም ኮርጆ ነው ለቱ መቀመጫ ፣
አባት ኮረብታ ነው ለልጁ ማመጫ ።

ዐእኔ ቤት እንዲህ ነው የናንተን አላውቅም ፣
እናትና መርፌ ሁሉን የሚጠቅም ።

በፈጠሮሽው ፍጡር በሠራሽው ዓለም ፣
ክናትነት ሴላ የጠላሁት የለም ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

ቻነቡ ጎጆዉን እፋፍ ላይ ሠርቻት ፣
ዘመም ዘመም አለች ስፍራም አልተመቻት ።

ካቨዋ ላይ ፈስሶ ጨፍ እይታፈስም ፣
ሠላሳ ዓመት ቢኖር ቂም አይበሰብስም ።

እረ ተው ተመለስ እሱ ነው ድንበሩ ፣
የጀግኖች መኖሪያ እይነካም በሩ ።

ገዳይ በየጉራው በየሸንተረሩ ፣
ይፈለግ የለም ወይ የእዳኝ ውሻ ዘሩ ።

ጮቄው ተመንጥሮ ይታያል አሰቱ ፣
የሀገሬ ጀግና የነደለበቱ ።

ተንኩለኛ ምጣድ በጀርባዬ ዞሮ ፣
ለካ ጥላት ብቻ ሆኖለሁ ዘንድሮ ።

ትንሽ ዝናብ መጥታ ጉም ያላስከተለች ፣
ትንሹን ትልቁን አስተዛዝባው ሄደች ።

አዳኙቱን ድመት አይጪቱ በላቻት ፣
እም ብላ ቀረች ቦታ ባያመቻት ።

ላሞቹን ንዳቸው ወደ በልጉ መሬት ፣
የሰው ቢት እንጀራ ይላል እሬት እሬት ።

ተጉዞ ተጉዞ ሰው እንደ ደመና ፣
መመለሻው ጠፋው ያነሩ ጉዳና ።

አይዞሽ ምንሽሬ እንንኩ ሻኩ ሽ ፣
ጥይት ካላለቀ ጥዬሽም አልሸሽ ።

እሀ ብለው ብለው እንተቴ ደረሰ ፣
አክ ብለው ወጣ ይም እየለበሰ ።

ላሞቹን ንዳቸው አቧራው ይነሣ ፣
ይከተል የለም ወይ አውራው እያነሣ ።

ወይ እኔን ውለጅ ወይ ሂጂ ከሰው ፣
ተገጠበ እራሴ ሲነድኝ የማከው ።

ነገረኛ ውኃ እታች ቢቆሙበት እላይ ይፈረሰ ፣
ጠላት መች ይተኛል ጥይት ካልቀመሰ ።

እሞራ በሰማይ ትዞራለች ጭላት ፣
ላይዘነጉ ይበትላል ዐረምና ጠላት ።

ጮቄው ታርሶ ታርሶ አበቀለ እንግጫ ፣
እንበለው ጠላትን አንሁን ማላገጫ ።

ሁለት ወንድማማች ወደ ወንዝ ወረዱ ፣
ወንድም የለሌውን እንደ ፍየል ሲያርዱ ።

እባክሽ እናቴ ውለጅ መንታ መንታ ፣
ቀኝ እጂን ብመክት ግራ እጂ ተመታ ።

በል ግፋ በል ግፋ በል ግፋ ጨምር ፣
ያልፋል ባንድ ሳምንት ችግርና መር ።

በሰፈው አውድማ የተብጠረው ፣
ገለባው ሄዶ ነው ምርቱ የቀረው ።

እረጅሙ ሲያጥር ጥቁሩ ሰው ሲቀላ ፣
ጥይት ቮልካ ስትሄድ በሰውዬው ገላ ፤
ልብ እይታመንም እንኳን ባልንጀራ ፣
ክፉ ጥል ክፉ ነው ክፉውን እይፈራ ።

ክፉ ጥል እምጥቶ እራሱን እያችልም ፣
እነካክቶ ሄደ ያንንም ያንንም ።

አሁን የከፋው ሰው ምን ምኑን ይያዛል ፣
አልቢኑን እንደሆን እንግቢት ይጓዛል ።

ላሚቱ ላም ወልዳ ነብር በልቶባት ፣
እምቢ እምቢ ትላለች እየንደጻት ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

በሬው ጥሻ ወልዶ ተንጋሎ ይልሳል ፣
የተበላ ገንዘብ መቼ ይመለሳል ።

እናንተም እለፉ እኛም እናልፋለን ፣
ጭው ካለው ሜዳ እንገናኛለን ።

አባይ ታረሰ አሉ በጥቋቁር በሬ ፣
ማሽላ ሲዘሩት ይበቅላል በርበሬ ።

አባይ ጉደል ጉደል ቀጭን መንገድ አውጣ ፣
የክፋው ወንድ ልጅ ተሻግሮ እንዲመጣ ።

ገፋ ገፋ እደርገህ ውጣ ካቀበቱ ፣
ልብ ያሰበው ነገር አይቀርም በክንቱ ።

ሆሆ በለው ንቡን አስጠጋው ከገደል ፣
ወተት ይሸፍታል እንኳን ሰው ሲበደል ።

እረ ሎጋ ሎጋ ስሙ ነወይ ሎጋ ፣
በደም ካልበከሉት እንደ እመዓት አልጋ ።

አንች የውጋዴ እሞራ ልጠይቅሽ ወሬ ፣
የጀግናቹ ጉራ እንዴት ነው አገሬ ።

እቲህ ሰው ነኪዎች ሰውን እየነኩ ፣
ቅንሽ ሲነኳቸው ይላሉ ባምላኩ ።

እሞኝ እሞኝ ውሉ እሞኝ ሲያድር ነወይ ፣
ሞርቶ ለፍቶ መብላት ጤና ላይሆን ነወይ ።

ወንድ ልጅ ተወልዶ ካልሆነ እንዳባቱ
እመልማሉ ስጡት ይፍተል እንደ እናቱ ።

እሙን እሙን አሉ ተዋቸው ይሙን ፣
ቢፈሩን አይደል ወይ የጠረጠሩን ።

እባክሽ እናቴ አታልቅሽ ብያለሁ ።
እገሬን በደሜ እጠብቃታለሁ ።

ታርሶም ተነግዶ ይሄ አለ ብለህ ፣
እንደምነሽ ጥይት የጀግኖች እዝመራ ።

ባባቱ ባድማ የተኛውን በሬ ፣
ቀስቅሰው ቀስቅሰው አያረጉት አውሬ ።

ቤቴን ከባኤሩ ካረንቋው ሠርቻት ፣
አለች ወጀጅ ወጀጅ ስፍራው ባይመቻት ።

ፉግር ፉግር እርን ይተኛል ነብር ፣
ጉበዝ አሳዳሪ እንደምነው ጦር ።

ባጭደው ብከምረው እበላው ይመስል ፣
ወይ ነገር ይመጣል እንዲህ ስል እንዲህ ስል ።

ምንሽር ለወንድም ቤልጅግን በእጅ ይዞ ፣
ቢሄዱት ምን አለ ዱሩን መንገድ አድርጎ ።

እረግ እትነካኩት ክፍት ይደር ጉበኑ ፣
የት ሄደ ቢሏችሁ ክፍቶት ሄደ በሉ ።

እትበል ውኃ ውኃ ከደምህ ጠጣለት ፣
በጦር የሞተ ሰው ሀኑንም የለበት ።

ወላውሌው እውደልዳይ እያወላወለ ፣
ጠላቱን ሰደደው ነገ ዛሬ እያለ ።

እትኰትኩች ዱሬ እትቁረጭ ዱሬ ፣
እገባብሻለሁ የትም የትም ዞሬ ።

ጠንከር ጠንከር በሉ እንውጣው ገደሉን ፣
የክፋው ወንድ ልጅ እይረሳም በደሉን ።

ጊዜው አልቆ ጊዜው ተገባዶ ፣
እዲስ አምቻና ሽውከኛው ተወዶ ።

ጅናው ወፍራም በሬ ዝምብ አይከለክለም ፣
እይጠቅም ጎደኛ ሬሳ እያስጥልም ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

እንተ የናት እገር ብሳናው ውልከፋው ፣
አታሳድርም ወይ ወንድ ልጅ የከፋው ።

በኃራራ እንጀራ አይበላም ስራጁ ፣
እባቱ ሞቶበት ተንገላታ ልጁ ።

በፈዎቹን መርጠህ ወደ ላይ በላቸው ፣
መጡብን ከግለት እንሂድባቸው ፣
እነሱ አውሬ አይደሉም እንደኛ ሰው ናቸው ።

እኒያው መጡ ደረሱ እዚያ ማዶ ፣
እየሸሹላቸው መከተል ተሰምዶ ።

የወንድ ልጅ እናት ታጠቂ በገመድ ፣
ልጅሽን አሞራ እንጂ አይቀብረውም ሀመድ ።

ነጭ አሞራ በሮ ይገባል ከዋኛ ፣
ያገርህን ጠላት አሳጣው መድረኛ ።

በፈው ጥጃ ወልዶ ተኝቶ ይልሳል ፣
ጠላት ባምላክ ቢሉት መጅ ይመለሳል ።

ላሟ ጥጃ ወልዳ ነብር መስዶባት ፣
ዞራ ዞራ እያየች እየነደዳት ።

ዘንድሮስ ለጉዴ ቁመቷም ረዘመ ፣
ያም አገር ያም አገር ይታየኛ ጀመረ ።

አፍርሷት ጎጇቱን ቁንጮዋን ይዛችሁ ፣
መጅም ቤት አልሠራ እናንተ ካላችሁ ።

ተው ና በለኝ ጥራኝ አገሬ ግራና ዬሩ ጉራንጉሩ ፣
ለአንተም ይሻልሃል ብቻ ውሎ ብቻ ከማደሩ ።

አይዞሽ ምንሽሬ አልሰጥሽም ለሰው ፣
አምስቱን ስድስቱን ዐፈር ሳላለብሰው ።

ጉራው ተለብለበ ሲታይ ሲጠየቅ ፣
እንዴነሽ ምንሽር የጉበዝ መብራቱ ።

አንጋዳ ነው ኡጋዴ አንጋዳ ነው ይውጣል መራቱ ፣
ጠላት እንደ ፍየል የታረደበቱ ።

ተንኰለኛ ፍየል ልቡ ያበጠበት ፣
እንዋጋ ብሎ በንብሩ ላከበት ።

ጮቄው ታረሰ እሱ በተጫዉን ሞፈር ፣
የሰው ቤት እንጀራ ይላል ዐፈር ዐፈር ።

ዝንብ ቢሰበሰብ አይከፍትም መግላሊት ፣
አይገኝለትም ለፈረ መድኃኒት ።

ካገራችን ዋልካ ጭለማ ጣሰበት ፣
እንሻገርና መብራት እናብራለት ።

ጀግናውን ጮቄ ላይ ሙቶ አገኘሀት ፣
ጠላት አይቶ መሸሽ ነውር ሆናበት ።

እረ ተው ተመለስ እሱ ነው ድንበሩ ፣
አባት ያበጀውን ታረርሳለህ እሱ ።

እውልኝ የኋላ ፣ ከፈለሰ ወዲያ ጨፍ አይለቀምም ፣
ይዘገያል እንጂ ያሰቡት አይቀርም ።

ይኼው ሄደ ንቡ መሄድ የለመደው ፣
ድንጉሉ ቀረ እንጂ የማይናደፈው ።

የንብሩን ጉሮሮ ፍየል ገብቶ ላሰው ፣
ያንበላውን ሜንታ ድመት ተንተራሰው ፣
መጠታቱ አይቀርም ወንድም የሌለው ሰው ።

ወንድም የሌለው ሰው ጥላው ከውካዋ ነው ፣
ክንፉን ከተመታ አሞራ ምን አለው ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

በድንጋይ ቢመታኝ መታሁት በኩበት ፥
አሁን ምን ያደርጋል ካለወንድም ጉልበት ።

እገር ሰላም ሲሆን ጀግና አይወደድም ፥
ያንበሳን እሬሳ ጅብ አይራመድም ።

እዚያው ቱኑ እናንት ሰዎች እረ እዚያው ቱኑ ፥
ከናንተም ይሞታል ከኛ ስትመጹ ።

ዲሞፍተር ሥራህን ያየ ሰው ይንገረኝ ፥
ምንሽር ሥራህን ያየ ሰው ይንገረኝ ፥
ተሸካሚው ሁሉ ከሚያንገራግረኝ ።

ምስለኔው ቀንጣፋ እጥቢያው ሰሎማ ውሻ ፥
ባደግንበት እገር አሳጣን መድረሻ ።

ጭላሊት ስታረጅ ትወልዳለች ጉጉት ፥
ያሳዝናል ጉበዝ በእንሩ ሲዋትት ።
ቡታያ ነው ብለው ኩበት ቢንዱበት ፥
ይችግር የለም ወይ እንጎት የለየ ለት ።

ጠጥተህ ጠጥተህ እንደ በርበሬ ፍል ፥
ወይት ትሄዳለህ ዕዳህን ሳትከፍል ።

ቀንዝ ብለው ይጓዛል የግዱ ፥
ያገሩ ጉዳና ሲጠፋው መንገዱ ።

ገዴ ዙራ ዙራ ከእንቀላሏ ላይ ፥
ቀን የጠበቀ ሰው ጅል ይባላል ወይ ።

እረ ጉዱ በዛ እረ ጉዱ በዛ ፥
በኩርማን እንጀራ ሰው እየተገዛ ።

እረግ አንቺ አሞራ ልጠይቅሽ ወሬ ፥
ባባቴ ባድግ ተጠምዷል ወይ በሬ ።

ጣሊያን እንጨት ልቀም ጀርመን ውኃ ቅዳ ፥
እንተው ሞረሀ ሞረሀ ባመጣሽው ዕዳ ።

አርሶ ያለመብላት ተሰሶ መሳት ፥
ቆይቶ ይገርፋል እንደ እግር እሳት ።

አልሞተ መስሎታል እሬሳው ባይወጣ ፥
ያባቴን ባድግ ሲነሬሉት በጣ ።

እንቱ ልለው አንቺ ልለው አስቸገረኝ ያ ሰው ፥
ነገር እንደ ወንፊት የሚያመላልሰው ።

የጠላ ዕለት ወኔ ለጦር ዕለት አይሆንም ፥
ከበረሃ ወርዶ ጋን አይነቱ ልም ።

እረ ምን ሞኝ ነው ጠላቱን ንግግር መንግቱ ፥
እየሣቁ መግደል ሳለ መድኃኒቱ ።

እንረስ ካላችሁ ተባብረን እንረስ ፥
እንረስ ካላችሁ ተውት ዳሞ ይልበስ ።

ተንኩለኛ ፍየል ተንኩል ፈልጋለች ፥
ከነብር መይብር ገብታ ተኝታለች ።

ካባይ ወዲህ ማዶ ቀጨማሽ ለምለም ነው ፥
ንቅል ንቅል እርጎ የሚወስድሽ ማነው ።

እህ ይላል እንጂ ምስለኔ አይዋጋም ፥
እንዴኔሽ አገሬ የታጠርሽው ባጋም ።

አረዱ አሉ በሬ እኛም ጥጃ እንረድ ፥
አፋችን ባይበላ እጃችን ደም ይልመድ ።

እረ ቀን አማኑ ቀን አማኑ ፥
አንድ ላይ ይውላል በሬውና ላሙ ።

አሁን ምን ብለው ነው ሊመሽ የላኩበት ፥
ጉልበቴን ካመነ ቢቀር ምናለበት ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

ምን አባት አለና ልጅ የሚያደራጅ ፣
አርፍን አሰባልቶ ና እንካ አረስ ነው እንጂ ።

እረ ምን ቢመፍር ምን ቢሰባ ለፈረስ ቀንድ የለው ፣
አሥር ሰው ቢመክት ለፈሪ ልብ የለው ።

ያርሶ ማንጐራጐር ልማዱ ነው ድሃ ፣
እየከረሰሰው እየቀዘቀዘው የሚጠጣው ውኃ ።

አባይ ሲደፈርስ ተከዜ ሲሞላ ፣
መድፍ አልፎ ሲጠመድ መትረየስ ሲያጓራ ፣
እርሳስ ቮልካ ስትሄድ በየሰዉ ገላ ፣
ልቦና ይከዳል እንኳን ባልንጀራ ።

እንድ በሬ ነበረኝ እንደኔ የከፋው ፣
ሥራ ውጣ ቢሉት ጭዱን ካፉ ተፋው ።

ላዳኑም ወንፈቱም ተጠራቅሟልና ፣
የምታበዋረው ጐራውና ጐራውና ።

ከማሽላ ጠላ ዘንጋዳ መርዝ አለው ፣
ካንድ እናት ተወልዶ ፈሪና ጀግና አለው ።

ባልንጀራው ሞቶ ይገላ ሲያለብሰው ፣
ተራምዶ ይሄዳል እንደማያውቀው ሰው ።

እሱ ጥቁር ወፍጮው ጥቁር ፣
እደባባይ ውሎ የሚያስኘው ዱር ።

የሚስቱ ውሽማ ሳላውቀው ያውቀኛል ፣
ነግጄ ስገባ ቀናህ ወይ ይለኛል ።

ልብሴም ራቷን ፈጀት ዘመድ እንደ ሞታት ፣
ባይረባባ ጀታ ብታጠቅ ብፈታት ።

ዘመድ ምን ዋለልኝ እገር ምን ዋለልኝ ፣
እንገቴን ብደፋ ጉልበቴ ቻለልኝ ።

አይቼው አይቼው ብለሃው ጉልበቴን ፣
መልካም ታርሶልሃል ብዬ ሄድኩ ቤቴን ።

የብቅል ኮርቻ የጊቾ ልጓም ፣
ዋንጫ ሲጨብጡ የማይዋሽ የለም ።

ምንሽሩን ስጡት ቢልጅጉንም ስጡት ዛላው ን እያዩ ፣
ወንድ ይውን ጅል ይውን እሞቱን ላያለዩ ።

እናቴም ደህና ዋይ እቴም ደህና ሰንብች ፣
ሚስቴ ከልሽን እንሺ አክቺ በዋመድ ፣
እንድ ላይ አይገኝ እንጂራና ዘመድ ።

የከፋው ሲያቅራራ ይመስላል ያበደ ፣
ማንም ሲናገረው ልቡ እየነደደ ።

እየልኝ አገሬ እየልኝ ወንዜ ላልጥለው ሲጥለኝ ፣
ሥሥት ሺህ ዓመቴ ትግል ከጀመረኝ ።

ከፋኝ ሞቴን ስጠኝ ወይ ዕድሌን ባርከው ፣
ሆዴ ሲነደል ነው እየከፋኝ ሳከው ።

መላሱን እንደ እባብ እያወጣወጠ ፣
ይቀዳል በጥይት ልቡ የቄረጠ ።

ሲሙቱት የሚዋት ጅል ጠላት ተገኝቶ ፣
ይቅር ብለን ተውነው ጓዛችን በርክቶ ።

እሞራ ነው ጀግና ነው የወንድ ልጅ ቁሱ ፣
እራስጌ ይቆማል እስኪወጣ ነፍሱ ።

ሲሄድ ውሎ ሲሄድ ያድራል ውኃ ፣
አታጥሎት ይሄዳል የመረረው ድሃ ።

እረ እንደምን አያቶ እንደምን ስለለኝ ፣
ቤት እሠራለሁ ስል ሰምቶኛል መሰለኝ ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

እረጅም ዛፍ እይቶ ይሰቀላል ቀር ፣
አሻግረህ ንደፈው በረጅም ወጨር ።

እረ ይትር ጎጆ እረ ይትር ቤት ፣
ይከበር የለም ወይ ሲወጣ ጠላት ።

ተው ተመለስ እረ ተው ተመለስ እንተ ነጭ በሬ ፣
ተጠመደ እይፈታም የጦቢያ ገበሬ ።

በጥዋት ጥመደና በጊዜ ፍታቸው ፣
የሰው እገር በሮች እራትም የላቸው ።

እንቆቆና እራት አስደቀሺ ጠጣሁ ፣
እኔ እንደ ሰው ነገር የሚመረኝ አጣሁ ።

መያዝ ምንሽር ነው ማስከተል ወንድም ነው ፣
ባይድና ሙታንታ ገፀና ገላጭ ነው ።

ተው በሱት ያንን ሰው መካር የለውም ወይ ፣
ምላጩን ተሳቡት እርሳሱ አይደለም ወይ ።

አጋማመሩና እርጥቡን ከደረቅ ፣
አዚያው ጢሶ ጢሶ አዚያው ነዶ ይለቅ ።

ባለቅሰው ባለቅሰው ጥብቆዬ ራሰ ፣
ካምናው ከራሞቱ የዘንድሮው ባሰ ።

እኔን ከፋኝ እንጂ አገሬን መች ከፋው ፣
አበቀለ ግራር ዝሆን የማይገፋው ።

እንድጅበት ቄስቀሺበት ካልጋመ አይጋገርም ፣
ወንድ ልጅ ካልከፋው አያንጉራጉርም ።

ወይ ዕድሌን ባርከው ወይ ቀኔን እድርሰው ፣
እንኳንስ ለራሴ አስቮገርኩኝ ለሰው ።

የጌቾ ለት የጠላ ለት ያፍ ወዳጅ አይገድም ፣
የቀሩጡ ለት የውሉ ለት ያው ወንድም ያው ወንድም ።

ጊዜው አልቆ ጊዜው ተገፍ ፣
ዋሾ መሬትና ሽውከኛ ተወዶ ።

በዚያም በዚያም ዘልቆ ካላሱት ሃይ ሃይ ፣
ደንጓዩ ቀዳዳ ነው ያስበላል ተባይ ።

በሬውንም ቢያርዱት ይገዛል መልሶ ፣
ቤቱንም ቢያነዱት ይሠራል መልሶ ፣
እሱን ገስ መሄድ ሰሌን እንተርሶ ።

እረ ጉድ ይገርማል ተገራሚ ቢገኝ ፣
ያመኑት ጓደኛ ጠላት ሆኖ ሲገኝ ።

እንጀራ አለ ብለው አይንግሩም ለድሃ ፣
ተሻግር ይሄዳል እርባ አራቱን ውኃ ፣

እሪ በሉ እሪ በሉ እሪታው ይበጃል ፣
ይዋል ይደር ማለት ጠላት ያደረጃል ።

በዚያ በበረሃ የዋልነው ከርከር ፣
አልቢኑ ዳኛ ነው ጥይቱ ምስክር ።

ጋራው ፈርሶ ጋራው ቢደለደል ፣
ያን ጊዜ ነበረ እዋሻኪን መግደል ።

እረ ተው እረ ተው እታመንታ ጉበዝ ፣
እይቁርጥም ጎራዴ ገና ሳይመዘዝ ።

ጉራው ጉራው በሉ በያላችሁበት ፣
ባላጋራ እይተኛም መሬት ሲለቀለት ።

የኢትዮጵያ ገበሬ ሞፈር መቀረጥ ያውቃል ፣
ካልተለበለበ መቼ ይታረቃል ።

ተው በሱት ያንን ሰው ምንዋ ዘንድር ፣
እሳት ሊበላው ነው በገዛ እጁ ሞሮ ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

አቅራራ ይሉኛል ምን ብዬ ላቅራራ ፣
እራሴም ሸብቷል እንደ ቆየ እንጀራ ።

እይዞሽ የፈረ እናት ልጅሽም ይህና ነው ፣
ካንዱ ቤት እንዱ ቤት ወሬ አመላላሽ ነው ።

እንድዱበት ቄስቊሱበት ካልጋመ አይጋግርም ፣
ቤትን መሥራት እንጂ ማፍረስ አይቸግርም ።

ፈረን እንሂድ ሲሉት እምቢ ብሎ ቀርቶ ፣
ሴቶች ደበደቡት ማባለቻ ደፍቶ ።

ጉበዝ ይሙት ፈረ ይኑር ቢሻው ፣
አተላ መሸከም ይችላል ትከሻው ።

በሬውን እረደው ቤቱን እርገው እመድ ፣
ሲጨንቀው ሲጠበው ያደርግሃል ዘመድ ።

አምናም ወልዳ ነበር ዘንድሮም ኢጋቶች ፣
መች ጤና ይገኛል ያች ላም ካልሞቶች ።

ኮሶ ለታየው ሰው መድኃኒቱ ኮሶ ፣
ግጠማት ነው እንጂ መልሶ መላልሶ ።

እየልኝ በኋላ ላልጥለው ሊጥለኝ ፣
ብዙ ዘመኑ ነው እኔን ሲሰልለኝ ።

ወንድሙን ሲከፋው ወንድሙን ካልከፋው ፣
እንጋለህ እረደው ደሙ እንዲከረፋው ።

የከፋው ወንድ ልጅ ለምን ሞት ይመኛል ፣
ድንጋይ ተንከባሶ ይልዳል ያገኛል ።

እረ የሰው ሆዱን አሁን ማን ያውቀዋል ፣
ወንዱ ልጅ ወንዱን ልጅ ለምን ይንቀዋል ።

ዓይኑ ትላልቅ ነው ሴት መገላመጫ ፣
ቁመተ ረዥም ነው ቋንጣ መሸምጠጫ ፣

ጣቱ ረጃጅም ነው የፍትፍት መዋጫ ፣
ጉበዞች ሲመጡ አለው መሸጉጫ ።

መረረኝ እንደ እሬት በላኝ እንደ ሳማ ፣
አይረባባ ነገር ጀሮዬ እየሰማ ።

በላኝ እንደ ሳማ መረረኝ እንደ እሬት ፣
ጀግና ጀግናውን ሰው እየበላው መሬት ።

አባቱ በፊ እርዶ እናቱ ቀትላ ፣
እቱ እየመተረች እያለቸው ብላ ፣
ቀዝቃዛ ነው ወኔው እንደ ዋርካ ጥላ ።

ተነሶ አስተነሶ ይገባል መሸሽ ፣
እንዱት ወለል ወለል ጉና ሴትንፋሽ ።

እስቲ ሳቡ መሸ እንወጣው ገደሉን ፣
ወንድ ልጅ ካልሞተ አይረሳም በያሉን ።

አሁን ማን ያውቀዋል ያገሬን መንገድ ፣
ጀርት የበላው ዱባ አድርጌው ብሄድ ።

ካልገደደ እውሬ ነብር አታድኑ ፣
ደሙን እየፋረ ይመጣል ወንድሙ ።

ያንበሳውን እናት ድመቷ ይብድባት አወይ አለመሆን ፣
ልዩዋ የመጣ እንደሁ ወዴት ልትደርስ ይሆን ?

እንተ ጠብ አትውደድ እኔ ጠብ አልወድም ፣
ሲቀር እያየኸው አገርና ወንድም ።

ፋሲል ጎጃ መስሎኝ ለካስ ግንብ ነው ፣

ዊተነሱ.....ቢያስተነሱ.....የማይናደው ።

እባብ ገላው መልካም አፉ ላይ ነው መርዙ ፣
ከማይረባ ሰው ጋር ንግግር አታብዙ ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

ፍየል እሳት ወልዳ እንዳትልሰው ፈጀች ፣
እንዳትተወው ቄጫት ፣
እወይ የኛ ነገር ዘወትር እመጫት ።

እረም አልተባለ ከረትም አልተነዳ ፣
የነደደው ጉበኔ ይገድላል ማለዳ ።

እንኳን እበረሃው ብትወጣ ሰማይ ፣
ያገራ ልጅ ጀግና ይለትሃል ወይ ።

እሳት ቢያዳፍኑት ይመስላል የጠፋ ፣
እውነት ይመስልሃል እንገቴን ብደፋ ።

የረጂም ምንሽር ተሰሶም እረጅም ነው ፣
ከተጣሉ ወዲያ እርቁ ለምንድነው ።

ንብር ገደል ገብቶ ፍየል ጉበኝችው ፣
ምነው የጓላዋን አዙራ ባየችው ።

እረ ጊዚው ዞሮ ጊዚው ተዘዋውሮ ፣
ፍየል ትሰብሳለች የንብሩን ጉሮሮ ።

እኔው ተበድዬ እኔው ራሴ ክሼ ፣
ውሽልሽል ነው እርቁ ላፍርለው መልሼ ።

መሄዴ ነው መልቀቂ ነው ካገር ፣
እንትቡም ሰፈዴም ነካካኝ በነገር ።

እረ ተወኝ ልቤ ደርሶ መደንገጡን ፣
ሞት እያቀርም ብዬ ነግሬህ እርግጡን ።

እንኳን የኛ ጎጆ የኮሸሸሉው ፣
ይፈርሰው አዳራሽ ባለምሰሶው ።

አገራችን ደንቢያ አገራችን ሰሜን ወሬ ጠያቂ ነው ፣
ምን ሰማችው ቢሉን ምን ሰማን ልንል ነው ።

አቡቲ ላሙን ልንዳው አቧራው ይነሣ ፣
ይዘኮል የለም ወይ ኮርማው እያገሣ ።

እረ ወርኃ ሞኙ ቆላ ሞኙ ሳያብብ ያፈራል ፣
እንዴን ካልገደሉት ሌላው መች ይፈራል ።

እንች ሞኝቴ እናቴ ወተት የሰጠሽኝ ፣
አውን እንዴት አርጎ ይገፋው ብለሽኝ ።

አልጋው ፈርሶ አልጋው ሲደለደል ፣
ምን ጊዜ ነበረ ምስኑኔውን መማደል ።

እኔን የቸገረኝ የጥይቱ የብረቱ ነገር ፣
ከዱር አይቄረጥ እንደ ጎጆ ማገር ።

ዲሞፍተርህን ይዘህ እርገው ገለል ገለል ፣
ሞት እያተርምና በጀርባ መጋለል ።

ተጉዞ ተጉዞ እንደ ጆሌ እሞራ ፣
መመለሻው ጠፋው ያገሩ ጉዳና ።

በሉ ጨምሩበት በበደል ላይ በደል ፣
ወተት ይሸፍታል እንኳን ሰው ሲበደል ።

ኮርሶም ተሸምቶ ይበላል እንጀራ ፣
እንደምነሽ ጥቃት የሞት ባልንጀራ ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

የጀግንነት ግጥሞች

ከጻንት ውሎ ከዘብጥ አዳሪ ፣
ሻሽ የመሰለ ድግ አስተርታሪ፣
ለናት አገሩ ተከራካሪ ፣
የሰው ኮርቻ ጠም አሳዳሪ ፣
ነፍስ የሚታደግ እንደ ፈጣሪ ፣
ከፈሳ ነዶ ከምር ከግፊ ፡
ልቡ ፣ የሳት ልብ ልብ አበዳሪ ፣
የፈረሰ ጦር መልሶ ሠሪ ።

አልበላ ሥጋ አልጠማ ጠጅ ፣
ጥጋበኛ ነው ይይዛል ፈንጅ ።

አንተ አቅናንር አሱ ይናንር ፣
ጥበበኛ ነው ያመጣል ነገር ።

አሳቱን አሳት አየወለደው ፣
አፍ አፍ አያለ አያነደደው ፡
ይጓዛል ገድሉ ይም የለመደው ።

አፍስ አፍስ ነው በለፈ ድግር ፣
አሥራቱ ለሹም የሚያደናግር ።

ባትዋጋ አንኳን በል አንከፍ አንከፍ ፣
የጋሻው ትሉ ትጓኑ ይርገፍ ።

ጉድ ጉድ ባይ እንደ ጨው ይቋሽ ፣
ቶኛ አጄ ታም በግራው ተኳሽ ፣
አልፎ ተሠሪ እንደ እንቁጣጣሽ ።

በፊ ገራፊ ባሊስ ቀበቶ ፣
አባቱ አልሰጠው አሱ አበጅቶ ።

አባቱ ነበር ዘንጋዳ ዘሪ ፣
ልጁ ያረሰ ጥይት ዘርዛሪ ፣
ከጥይት ጥይት መርጠ ቀርቃሪ ፣
የቤልጅግ ጥይት በደም ነካሪ ።

ማነቆ ዛቡ ምራን ልባቡ ፣
ድግር እርካቡ ፣
የሎጋ ጌታ አርሶ ጠገቡ ።

አረ እንዳንድ ጊዜስ እምቢ ነው መልካም ፣
እንበሳ ጠጉሩን ገበንብ አያስነካም ።

አረ ምን ልሥራ አረ ምን ልውን ፣
ግራር ተልጠ ምንሽር አያዛን ።

የነዚያ መንድም የነዚያ ታናሽ ፣
በቡጢ ጥሎ በካራ ነስናሽ ።

ትልቅ ሰው ገዳያ ዘርክት ያለውን ፣
ልብሱ ለሽክም ያስችገረውን ፣
ተዝካሩ ሳምንት የሚበላውን ።

እ ት ት ት ብርድ ይሞቃል ወይ ፣
የጠሉትም ሰው ይናፍቃል ወይ ።

ደንጋይ ቢማግ አይቄረስም ፣
ወንድም እንዳያ ነው አይተመስም ።

ትሰጠኝ እንደሁ ስጠኝ ጠበንጃ ፣
አልቀበልም ኩሳሳ ጥጃ ።

ገዳይ ክቤቱ በታች ፣
እናቱ አያየች ሚስቱ አያወኳች ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

እናት አባቱ ያላሏደገው ፣
እንደ ዝንጀሮ ጭር ያደገው ።

እገሩ ወዲያ ሙጎል እንሷ ፣
ንፍስ አሳላፊ እንደ ሥላሴ ፣

እገሩ ወዲያ ሙጎል ደገሞ ።
ንፍስ አሳላፊ ደገሞ ደጋግሞ ።

እገሩ ወዲያ ሙጎል ፎገራ ፡
በቱባ ተያት የሚያንጠራራ ።

አባቱ ነበር የሰር ገበሬ
ልጁ ደረሰ የወይፈን በሬ ።

አባቱ ነበር ዳሮት ደጋሚ ፡
ልጁ ደረሰ በርሳስ አራሚ ።

አትለጀልጀኝ ወሌ መጣ ፣
በማጀት ልሂድ በበር ልውጣ ።

ድንጋይ ቢማማ በእጅ አይቁረስ ፡
ኃይለኛው መጣ ግሩም አይድረስ ።

እምቢኝ አለ አይሸኘም አለ ፡
ያባቱን አዝር አልለቅም አለ ።

ያባትን አዝር ለቀው ሲሄዱ ፡
ሻኖጣ በሬ እየጐመዱ ፡
አልፍኝ ካናራቯ እያንደዱ ።

ውረድ እንውረድ ጠሪድ ካለቁ ፡
ያምሳ ነኪታ ከሞላበቁ ፡
የጦሰው ሞተ ታልትስ እናቱ ።

ሾላ ቢወናር ከአጠገብ ይበቅላል
ዝርጠ ዝርጠውን እምጣልኝ ትግል ።

ካደባባይም ሦስቱ ይሙቱ ፣
ድሃ ሲበደል ዝም የሚሉቱ ፤
ከካህናቱም ሦስቱ ይሙቱ ፣
የሐሰት ስብከት የሚሰብኩቱ ፤
ከዳኞቹም ሦስቱ ይሙቱ ፣
ያለፍርድ ፍርድ የሚፈርዱቱ ፤
ከሽማግሌዎች ሦስቱ ይሙቱ ፣
ነገር እንደ ጦር የሚያሻዥቱ ፤
ከባልቴቶቹም ሦስቱ ይሙቱ ፣
የሰውን ትዳር የሚያፈርሱቱ ።

የዳኘው አሽከር የሳቱ ላንቃ ፣
የኰስትር አሽኮር የሳቱ ላንቃ ፣
የቆሙበቱ መሬቱ ነቃ ።

ጴብ ጴብ እንደ በረዶ ፣
በልጅነቱ በረሃ ለምዶ ።

ደርሰንባቸው ሳይታጠቁ ፣
እንደ ዝንጀሮ ፀሐይ ሲሞቁ ።

በተባበሱ እንደ ኮርቻ ፣
መተኰስና መግደል የብቻ ።

አባቱ ኩሩ ልጁ ወራዳ ፣
ባእጭር ምንሽር የሚያስከነዳ ።

አባቱ ነበር የድንበር ፈራጅ ፣
ልጁ ደረሰ በጥይት አራጅ ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

ሥነ-ቃል በንግርና በዜማ የሚገለጥ ያንድ ሕዝብ የረጅም ዘመናት ቅርስ ነው ። አገራው በሥነ-ቃሉ እራሱን ይገልጣል ፣ እሱነቱን ይፋ ያወጣል ። በዘመናት ሒደት ውስጥ እራሱን የሚ ያፈላልገውና መልሶም የሚያገኘው ከሥነ-ቃል ቅርሱ ነው ።

አድማሱ ደስታ ፣ « የማር እሸት » ብለው በሥ የሙት ጥውም መጽሐፋቸው ፣ ከአማርኛ ሰፊ የሥነ-ቃል ቅርስ — ከግጥሙ እኳያ — መጠነኛ የሆነ ስብ ስብ ሥራ አቅርበውልናል ። ያንን የብዙ ታሪካዊ ገድል ባለቤትና የእኛነታችን መዘክር የሆነውን ያለፈውን ዘመን ፡ የበደልና የጎዘን ፡ እንዲሁም የጀግ ንነትና የፍቅር መግለጫ በሆኑት የሥነ-ቃል ግጥ ሞች አማካይነት መለስ ብለን እንድንቃኝ አድርገ ውናል ። እራስን እንደማወቅና እኔነትን እንደማ ጽደቅ የሚያኩራ ነገር የለምና ፣ የአድማሱ ደስታ ጥረት ይበል የሚያሰኝ ነው ።

D AMH Adm
Admasu Dasta
Yamar esat 1988
ihvu 3
03010254791003